# በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ የሚፈፅሟቸው ስህተቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና፤ (በቀርሳ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ- ምረቃ መርሐ- ግብር

በ

ትዕግስት ታምሩ



ጥቅምት 2016 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ የሚፈፅሟቸው ስህተቶችናየስህተት ምንጮች ትንተና፤ (በቀርሳ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ- ምረቃ መርሐ- ግብር

አማርኛን ለማስተማር (TeAm) ማስተር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ትዕግስት ታምሩ

አማካሪ፡- ዶ/ር ጌታቸው እንዳላማው

ጥቅምት 2016 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ- ምረቃ መርሐ- ግብር

# በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ የሚፈፅማቸው ስህተቶችናየስህተት ምንጮች ትንተና፤ (በቀርሳ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ

ትዕግስት ታምሩ

አማካሪ፡- ዶ/ር ጌታቸው እንዳላማው

የፈታኝ ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም____________________ ፊርማ______________ ቀን________

የፈታኝ ስም____________________ ፊርማ______________ ቀን________

የፈታኝ ስም____________________ ፊርማ______________ ቀን________

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ የሚፈፅማቸው ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና (በቀርሳ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት) በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ- ምረቃ መርሐ ግብር አማርኛን ለማስተማር (TeAm) ማስተር ዲግሪ ማሟያ የቀረበው ጥናት፣ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ስም፡- ______________________

ፊርማ፡- ____________________

ቀን፡- ______________________

# ምስጋና

በመጀመሪያ ከሁሉ አስቀድሜ በህይወት ዘመኔ ሁሉ በቸርነቱ ለማይለየኝና ለዚህም ስኬት እንድበቃ ለረዳኝ ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው፡፡

በመቀጠል ባሉኝ ብዙ ክፍተቶች ሳይሰለቹ እየደገፉኝና ቀናውን መንገድ እያሳዩኝ ለዚህ ጥናት መሳካት ላበቁኝ መምህሬና አማካሪዬ ለዶ/ር ጌታቸው እንዳላማው ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

በማከልም ይህንን የትምህርት እድል በመስጠት እንድማር ለረዳኝ የአርሲ ዞን እና ለጥናቴ ማስኬጃ የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የላቀ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

በመጨረሻም አይዞሽ በርቺ እያሉኝ ባላቸው አቅም ሁሉ ጉልበት ለሆኑኝ ቤተሰቦቼ፣ ወዳጅ ዘመዶቼ፣ ልጆቼና የስራ ባልደረቦቼ ምድጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ እንዲሁም የሚያስፈልጉኝን መረጃዎች በመስጠትና ድጋፍ ላደረጉልኝ ለርዕሰ መምህር አቶ መርጋ ደራሮ፣ ም/ር/መ/ር ድርባ ዳባ፣ መምህር ንጉሱ ጥላዬ፣ መምህር ገብረ ማርያም ለገሰና ለሁሉም የቀርሳ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን እና ተማሪዎችን ድርሰት በማፃፍና የተፃፉ ድርሰቶችን እርማት በመስጠት ለተባበሩኝ አማርኛ ቋንቋ መምህራን ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡

# *አጠቃሎ*

*የዚህ ጥናት ዓላማ አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈፅማቸውን ስህተቶች እና የስህተት ምንጮችን መተንተን ነው፡፡ የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት በመረጃ መሰብሰቢያነት ያገለገሉ መሳሪያዎች በተማሪዎች የተጻፉ ድርሰቶች እና የመምህራን ቃለ- መጠይቅ ናቸው፡፡ መረጃዎች ከተሰበሰቡና አስፈላጊው አደረጃጀት ከተደረገ በኋላ በቲ- ቴስት ትንተና እና ገላጭ በሆነ መንገድ በመተንተን የቀረበ ሲሆን ከትንተናው የተገኘው ውጤትም  በቲ- ቴስት ስሌት ተሰልቶ8.35 መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም የተገኘው ውጤት የሚያሳየው መምህራን ከድርሰት ልምምድ በፊትና በኋላ የሚገኘው ውጤት የተሻለ መሆኑን ሲሆን ድርሰት ሲያፅፉ ግብዓት የሚሆናቸውን ትምርት መስጠት የሚገባ መሆኑን ነው፡፡ ተማሪና መምህር የማይለያዩ በመሆናቸውም የ9ኛ ክፍልን አማርኛ ትምህርት ሲሚያስተምሩ መምህራን ቃለመጠይቅ በማቅረብ ስለተማሪዎቻቸው ድርሰት የመፃፍ ችሎታና በሚፅፉበት ጊዜም የሚሰሯቸውን ስህተቶች የተመለከቱ ጥያቄዎች የቀረቡላቸው ሲሆን የተገነው መረጃ በሚገባ ተተንትኖ የተገኘው ውጤትም ሁኔታ ከስህተቶች በመነሳት ለዚህ ሁሉ ስህተቶች ምንጭ ይሆናሉ ተብለው ከሚታመኑት ውስጥ የቋንቋ ተጽእኖ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ፣ የመማር ማስተማር ሂደት እና የስነልቦናዊ ተጽእኖ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ በመጨረሻም ማጠቃያ እና የተከሰቱትን ስህተቶች ለመቅረፍ ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የመፍትሔ ሀሳቦች ቀርበው ጥናቱ ተጠናቋል፡፡*

# ማውጫ


ይዘት ገጽ

ማረጋገጫ ........ 1

ምስጋና........ i

አጠቃሎ ........ii

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ........ 1

1.1 የጥናቱዳራ........ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 4

1.3 የጥናቱ አላማ........ 4

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 5

1.5 የጥናቱ ወሰን ........ 5

1.6. የቃላት እና የሐረጋት ትርጓሜ ........ 6

ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳን........ 7

2.1 የስህተት ምንነት........ 7

2.2 የስህተት ትንተና ታሪካዊ ዳራ ........ 12

2.3 የስህተት ምንጮች ........ 16

2.2.1 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ........ 18

2.3.2 የውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ........ 19

2.3.3 የማስተማሪያ መሳሪያዎች እና የማስተማሪያ ዘዴ ድክመት........ 21

2.3.4 ማህበራዊና ስነ- ልቦናዊ ሁኔታዎች........ 23

2.4 የስህተት ትንተና ዘዴ........ 24

2.4.1. የስነልሳን ክፍሎችን መሰረት ያደረገ ክፍፍል........ 24

2.4.2. የአረፍተ ነገር ቅርጾችን መሰረት ያደረገ ክፍፍል........ 25

2.4.3. ንጽጽራዊ ክፍፍል........ 25

2.4.4. ተግባቦታዊ ተጽእኖ መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል........ 25

2.5 የስህተት ትንተና አስፈላጊነት........ 26

2.6 የቀደምት ስራዎች ቅኝት ........ 28

ምዕራፍ ሶስት

የጥናቱ ንድፍና የአጠናን ዘዴ ........ 31

3.1 የጥናቱ ንድፍ ........ 31

3.2 የትምህርት ቤት አመራረጥ ........ 31

3.3 የክፍል ደረጃ አመራረጥ ........ 32

3.4 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........ 32

3.5 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ........ 32

3.6 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 32

3.6.1 የተማሪዎች ድርሰት ........ 32

3.6.2. የመምህራን ቃለ መጠይቅ ........ 33

3.7 የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 33

3.7.1 የድርሰት ሲጻፍ ስህተቶችን አተናተን ........ 33

3.7.2 የቃለ- መጠይቅ አተናተን ........ 34

ምዕራፍ አራት

የመረጃ ትርጎማና ትንተና ........ 35

4.1. የድርሰት እርማት ውጤት ጥቅል ትንተና ........ 35

4.2 የቅድመና ድህረ ልምምድ የድርሰቶች ውጤት ቲ-ቴስት ስሌት (P<0.05) ........ 36

4.3 የስህተት ውጤት ትንተና ........ 36

4.3.1. የውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ ........ 37

4.3.2. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ ........ 37

4.3.3. የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶችና የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት ........ 37

4.3.4. ስነልቦናዊ ሁኔታዎች ........ 38

4.4 የተጠኚዎች የቅድመና ድህረ የድርሰት ጽሁፎች እርማት ዝርዝር ውጤት ትንተና ........ 38

4.6 ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተወሰዱ መረጃዎች ውጤት ትንተና ........ 40

4.6.1 ከስህተት ምንጮች አኳያ የተገኙ መረጃዎች ........ 40

4.6.2 ከውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ አኳያ የተገኙ መረጃዎች ........ 41

4.6.3 ከማህበራዊና ስነ- ልሳናዊ ሁኔታዎች አኳያ የተገኙ መረጃዎች ........ 42

4.6.4 ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ አኳያ ከተጠየቁ የተገኙ መረጃዎች ............................ 42
ምዕራፍ አምስት
ማጠቃለያና የመፍትሔ ሃሳብ ............................ 45
5.1 ማጠቃለያ ............................ 45
5.2 የመፍትሔ ሃሳቦች ............................ 45
ዋቢ መጻህፍት ............................ 47
አባሪዎች ............................ 50
አባሪ ሀ፦ ተማሪዎች የፃፏቸው ድርሰቶች የታረሙበት ወይም መምህራን ውጤት የሰጡበት መስፈርት ............................ 51
አባሪ ለ፦ የተጠኚዎች የቅድመና ድህረ የድርሰት ጽሁፎች እርማት ዝርዝር ውጤት ............................ 52
አባሪ ሐ፦ በተማሪዎች የተጻፉ ድርሰቶች ............................ 53
አባሪ ሐ፦ የመምህራን ቃለ- መጠይቅ ............................ 56

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የዚህን ምርምር ምንነት ለመገንዘብ እናለመረዳት የሚያስችሉ  ንዑሳን ይዘቶች ተካተው ቀርበዋል፡፡ በዚህም የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ መነሻችግሮች፣ የጥናቱ ዓላማዎች፣ የጥናቱጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን እና የጥናቱ ውስንነት  የሚሉ ጉዳዮች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ከአራቱ የቋንቋ መሰረታዊ ክሂሎች መካከል አንዱ የጽህፈት ክሂል ነው፡፡ የመጀመሪያው ቋንቋ ተናጋሪዎችም ሆኑ የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በመደበኛው ትምህርት ቤት ውስጥ ይማሩታል፡፡ በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ወቅት ጽህፈትን ተጠቅሞ ሀሳብን ለመግለጽ የቋንቋውን ሰዋሰው እና ማህበራዊ የቋንቋ አጠቃቀም ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ጽህፈት እንደማዳመጥ እና እንደመናገር ክሂሎች ለቋንቋ ተጋላጭ በመሆን ብቻ የሚገኝ ሳይሆን በአፈፈትም ሆነ በኢ-አፈፈት ተናጋሪዎች በሚያደርጉት ተደጋጋሚ ልምምድ እና ትምህርት የሚዳብር ነው፡፡

ተማሪዎች የማድመጥ፣የመናገር፣ የማንበብና፣ የመጻፍ ክሂላቸው እንዲዳብር፣ እንዲሁም የሰዋስውና የስነጽሁፍ እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው፡፡ የዚህ ጽንሰ ሃሳብ ዓላማ የአራቱን የቋንቋ ክሂሎች ማዳበር ሲሆን፣ የመማር አጠቃላይ ግቡም በአራቱ የቋንቋ ክሂሎች የተግባቦት ብቃት ላይ መድረስ ነው (Widowson 1978)፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች የሚተላለፈውን መልዕክት አድምጠው የመረዳት፣ የቀረበላቸውን ጽሁፍ የማንበብ፣ ሀሳባቸውን በንግግርና በጽሁፍ የመግለጽ እንዲሁም ደረጃውን የሚመጥን የአጻጻፍ ስርዓት ተከትለው ሀሳባቸውን በጽሁፍ መወከል መቻል በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ሊዳብሩ የሚችሉ ናቸው፡፡

የማንኛውም ቋንቋ ትምህርት ዋና ዓላማው የቋንቋ ክሂሎችን ማዳበር ነው፡፡ ይህን ተግባር በተገቢው መንገድ ለማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ ተገቢውን ትኩረት የሰጠ የትምህርት ይዘት አዘጋጅቶ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚቀርብ የክሂል ይዘት ለአንድ ክሂል የማያዳላ እና ሁሉንም በተገቢው መንገድ አጣጥሞ የያዘ መሆን ይኖርበታል በማለት Harmer (1992: 52) ይገልፃሉ፡፡

ከአራቱ የቋንቋ መሰረታዊ ክሂሎች አንዱ የመጻፍ ክሂል ነው፡፡ አማረ (1976) “የሰው ልጅ እውቀቱን፣ ሀሳቡንና ስሜቱን ለመሰሎቹ ለማጋራት የፈጠረው የጽሁፍ ጥበብ፣ በተለያየ

የአጻጻፍ ብልሀት የተቀነባበሩ ጽሁፎች የሰው ልጅ የታሪክ ሂደትና የስልጣኔ ቅርስ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፤ ይሁን እንጂ አንድ ሀሳብ ከአእምሮ ወደ ጽሑፍ በመቀየሩ ብቻ ከጻፊው ወደ ተደራሲው ተላልፎ መግባባትን ይፈጥራል ማለት አያስደፍርም" ሲሉ በጽሁፍ የሚቀርብ ሀሳብ አላማውን ከግብ እንዲመታ በጥንቃቄ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻሉ። የመጻፍ ክሂልን ተጠቅሞ ሀሳብን ለመግለጽ የሚተላለፈውን ጽንሰ ሀሳብ ከመገንዘብ ባሻገር የቋንቋውን ሰዋሰውና ማህበራዊ የቋንቋ አጠቃቀም ማወቅ ያስፈልጋል።

መጻፍ እንደማዳመጥ እና መናገር ያሉ ክሂሎች ለቋንቋ ተጋላጭ በመሆን ብቻ የሚገኝ ሳይሆን ተማሪዎች በሚያደርጉት ተደጋጋሚ ልምምድ እና ትምህርት የሚዳብር ነው። በመሆኑም ጽሁፉ አንባቢ ጋር ከመድረሱ በፊት የሚያሻሙ ሀሳቦችን ለማስቀረት ጥንቃቄ የተሞላበት ዝግጅትና በቂ ልምምድ እንደ ሚያስፈልገው ይታመናል። በርካታ ምሁራን Nunan (1989), Grabe and Koplan (1996), Mohammed (2008), Nacira (2010) እንደገለጹት የመጻፍ ተግባር ከሌሎች ክሂሎች ይልቅ ከባድና ውስብስብ ነው በማለት አብራርተዋል። በተጨማሪም ‹‹ምናልባትም ከአለማችን ግማሽ ያህሉ ሰዎች እንዴት በጥሩ ሁኔታ መጻፍ እንዳለባቸው አያውቁም›› በማለት (Grabe and Koplan 1996) ገልጸዋል።

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት የምሁራን ሃሳቦች መረዳት እንደሚቻለው መጻፍ ባለው ውስብስብ ባህሪ፣ እንዲሁም በትምህርትና በብርቱ ልምምድ የሚዳብር መሆኑ በመጻፍ ክሂል አስቸጋሪ እንደሆነ ነው።

በመጻፍ ክሂል ተግባር ወቅት ተገቢውን መልዕክት ለአንባቢው ለማድረስ የንግግሩን ድምጸት በትክክለኛው ትዕምርታዊ ምልክቶች መግለጽ ተገቢ ነው። ካልሆነ የተጻፈው መልዕክት አንባቢው ጋ ደርሶ የታለመለትን ግብ የመምታቱ ጉዳይ አስተማማኝ አይሆንም። በመሆኑም አንድን መልዕክት በጽሁፍ ለማስቀመጥ ስናስብ መጀመሪያ አዕምሯችን ውስጥ የሚመጣው የቋንቋውን አወቃቀር ስርዓት ማጤንና ተግባራዊ የማድረግ ጉዳይ ነው። እያንዳንዱ ቋንቋ የራሱ ህግ አለው፤ ይህንን ህግ ጠብቆ መገልገል ደግሞ መልዕክቱን በተገቢ መልኩ ያለመድበስበስ በማቅረብ እና ትርጉም እንዲኖረው በማድረግ ረገድ ሰዋሰውን ጠንቅቆ ማወቅ ትልቅ ፋይዳ እንዳለው መገንዘብ አያዳግትም።

ባየ(2000) እንደገለጹት ‹‹ሰዋስው›› ማለት ‹‹መሰላል›› የሚል ፍች የያዘ ነው። ይህም በአንድ ቋንቋ ውስጥ ከድምጽ መዋቅር እስከ ዓረፍተነገር ምስረታ ያለውን ስርዓታዊ ቅንብር

ይመለከታል፡፡ ከዚህም ባሻገር በቋንቋው ድምጾች የተወከሉትን ቃላት ትርጉም፣ እርስ በርስ ተሰናስለው የሚከስቱትን ትርጉም አዘል የሀሳብ ፍሰት፣ ፋይዳዊ የስርዓተ-ነጥቦችና አያያዥ ቃላት አጠቃቀምን ይመለከታል፡፡ በአጠቃላይ በጽሁፍ ውስጥ የሚከተቡት ትዕምርቶች ሁሉ አንዳች ክስተትን ለመከወን የተሰደሩ ስርዓታዊ ነጥቦች ሊሆኑ ይገባል፡፡

እንደ Richards and Schmidt (2002፣ 184) ገለፃ የጽሑፍ ስህተት ቃላትን፣ ሰዋስውን፣ ሥርዓተ ነጥቦችንና የአገላለጽ ሥርዓትን በተሳሳተና ባልተሟላ መልኩ መጠቀም ነው፡፡ Chomsky (1965) ይህን አባባል ሲያጠናክሩ ስህተትና ግድፈትንበቅደም ተከተል የብቃትና የአፈፃፀም ክፍተት ውጤት በማለት ይገልጿቸዋል፡፡ ብቃት የተማሪውን የቋንቋ ዕውቀትና ቋሚአጠቃቀምባህሪየሚመለከት ሲሆንአፈፃፀም ግን ተማሪው በክንውን ወቅት የሚያሳየውን የአንዴ ጊዜ የቋንቋአጠቃቀም ችግርን ያሳያል፡፡ ይህ የአንዴ ወቅት የቋንቋ አጠቃቀም ችግር ደግሞ የተማሪውን የቋንቋ ዕውቀት በተሟላ አያሳየንም፡፡ ስህተት ከፍታው ትክክል እየሰራሁ ነው" ብለው ሲከውኑ ስህተት መስራትን ካለመረዳት የዕውቀት ክፍተት አንጻር ስህተትን የመፈፀም ተግባር ይሆናል፡፡ ስህተት በስርዓት የተከወነ፣ ቀጣይነት ያለው፣ አፈንጋጭ የሆነና ምናልባትም በጥናት በተደገፈ ሳይንሳዊ ስሌት እስካልተወገደ ድረስ በተማሪው የመማር ሂደትቋሚ ባህሪይ ሆኖ የሚቀጥል ነው፡፡ በሥነ-ቋንቋ ዘዴ በተወሰነ የቋንቋ ትምህርትደረጃ የተለያዩ የስህተት ዓይነቶች በተማሪዎች ይፈፀማሉ፡፡ ይህንተረድቶየማስተካከያ እርምጃ የመውሰድ ሂደት በአንድ ተቋማዊ የቋንቋ ሥርዓት እስካልተመራ ድረስ ስህተቶች ባልተገባ የቋንቋ ክህሎት ማዳበር ሂደት እያደጉ ይመጣሉ James,C, (1998:77)፡፡

ከዚህ እንደምንረዳው ስህተት ተማሪው የድርሰት ሥራውን ሲያከናውን ትክክለኛው የአፃፃፍ ሥርዓት ይህ ነው ብሎ እየከወነ ባለበት ሂደት የሚፈፀም ነገር ግን ከቋንቋው አፃፃፍ ሥርዓት ያፈነገጠ ትግበራ መሆኑን ነው፡፡ በዚህ መሰረት ስህተትን ስህተት ሉያሰኝ የሚችለውን ደረጃ መለየት ተገቢ መሆኑንና የስህተትዋና መገለጫው የተማሪው ባህሪ ሆኖ ሊቀር የሚችል መሆኑን ማወቅ ይገባል፡፡

የመጻፍም ሆነ የሰዋስው ዋና ዓላማ ቋንቋውን በማዳበር ስርዓቱን የጠበቀና ስኬታማ የተግባቦት ሂደትን መከወን ነው፡፡ ‹የቋንቋ እውቀትን ማዳበር፣ የአወቃቀርን ስርዓት ጠንቅቆ ማወቅ፣ ለምን ምክንያት መናገርና መጻፍ እንዳለባቸው ጭምር በቂ ምላሽ መስጠት መቻል ነው (Harmer, 1989)፡፡ በጽህፈት አማካይነት የሚደረግ የቋንቋ ግንኙነት በዋነኛነት የትምህርት ውጤት በመሆኑ ከፊደል አጣጣል ጀምሮ ሊተላለፍ የተፈለገውን ጽንሰ-ሀሳብ መገንዘብ፣

የቋንቋውን ማህበራዊ አጠቃቀም ማወቅ፣ ሰዋስውንና የመጻፍ ሂደቶቹን በየደረጃው መማርና ክሂሉን ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

Corder (1967, 161-163) እንዳሰፈሩት "የስህተት ትንተና ጥናት አጥኝው/ዋ ስለ ቋንቋው ባህሪ ጠልቆ/ቃ እንዲያስተውል ወይም እንድታስተውል ይረዳዋል/ታል፡፡ በተጨማሪም ጥናት አድራጊው/ዋ ስለቋንቋ መማርና ማስተማር ስልት የበለጠ እንዲረዳና ወይም እንድትረዳ ቀድሞ ያለውን ዕውቀት እንዲያሻሽል ወይም እንድታሻሽል ይረዳዋል/ታል፡፡"

Wilkins (1974, 2004) በማከልም የስህተት ትንተና የማስተማሪያ መሳሪያም ለመገምገም እንደሚረዳ ይገልፃሉ፡፡

በዚህም መሰረት ቀደም ሲል የቀረቡትን መሰል ንድፈ ሀሳባዊ መሰረቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ጥናት አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ላይ ያተኩራል፡፡ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች የመግባባት ሂደትን ሊያሳዩን የሚችሉ በመሆናቸውና የስህተቶቹን አይነት እና ምንጮቹን ማጥናት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

አጥኚዋ ይህን ጥናት ለማከናወን እንድትነሳሳ ያደረገው ዋነኛ ምክንያት በኦሮምያ ክልል ለረጅም ጊዜ በመምህርነት ስታገለግል በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች እና በዚሁ ስህተት መከሰት ምክንያት ሀሳባቸውን በፈለጉት ልክ ለማስተላለፍ ሲቸገሩ በማየት ነው፡፡ 9ኛ ክፍል የተመረጠበት ምክንያት እነዚህ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ከማይነገርበት ከገጠሩ ማህበረሰብ ስለሚመጡ ለጥናቱ ጥሩ ግብአት ይሆናሉ ተብሎ ስለታመነበት ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዓላማ አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈፅማቸውን ስህተቶች መተንተንና የስህተት ምንጮችን መለየት ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ ከዚህ አጠቃላይ ዓላማ በመነሳት ለሚከተሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል፡፡

ሀ. ተማሪዎቹ ድርሰት በማጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው፡-

- ዋና ዋና የስህተት አይነቶች ምን ምን ናቸው?
- የስህተቶቹስ መጠን ወይም አይነት ምን ያህል ነው?
- ድግግሞሻቸውስ

ለ. ለዚህ ስህተቶች መከሰት ምንጮች ይሆናሉ የተባሉት ነገሮች ምን ምን ናቸው?

ሐ. ተማሪዎቹ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን የስህተት አይነቶች ለመቆጣጠር የመፍትሔ ሀሳቦች ምንድን ናቸው?

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

- በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ በማስተማር ረገድ ውጤተ ሊያስገኙ የሚችሉ ስልቶችን ለመምረጥ ይጠቅማል፡፡
- የቋንቋው መምህራን ተማሪዎቻቸው ሊፈጽሟቸው የሚችሉትን ስህተቶች የቀደሙት ተማሪዎች ካላቸው ልምድ በመነሳት አስቀድመው እንዲተነብዩ ያስችላቸዋል፡፡ ስለሆነም መምህሩ ተማሪዎቹ የሚፈፅሟቸውን የስህተት አይነቶች እና የስህተት ምንጮችን ካወቁ ወይም ከገመቱ ስህተቶችን ለማረም የሚያስችል የማስተማሪያ ዘዴ ለመቀየስ ያስችላቸዋል፡፡
- ባለድርሻ አካላትም በትምህርት ዓይነቱ ላይ ያለውን ችግርና ተጽዕኖ በመረዳት የመፍትሄ እርምጃ እንዲወስዱ ያስችላቸዋል፡፡
- ወደፊት በዚህ ርዕስ ዙሪያ ጥናት ለሚያደርጉ ተመራማሪዎች እንደመነሻና ድጋፍ ሰጪ መረጃ በመሆን ያገለግላል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በቀርሳ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ2015 ዓ.ም የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ በሚጽፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር፣ የሰዋስው አጠቃቀምና ከፅንሰ ሀሳቡ ጋር የተያያዙ ስህተቶችን

እና የስህተት ምንጮችን በመተንተን ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ትኩረቱም በተለይ በድርሰት ውስጥ ከሚፈጸሙ ስህተቶች ውስጥ ከፍተኛ የተደጋጋሚነት መጠን ያላቸውን ስህተቶች በመተንተን ዋነኛ ናቸው ተብለው የሚገመቱ የስህተት ምንጮችን በማብራራት ላይ ይወሰናል፡፡ ካለው የገንዘብና ጊዜ ውስንነት አኳያ በወረዳው የሚገኙ ሌሎችን ትምህርት ቤቶች አላካተተም፡፡

## 1.6. የቃላት እና የሐረጋት ትርጓሜ

ስህተት፡- ተማሪዎች በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የተፈጸሙትን የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም እና የጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ስህተቶችን የሚመለከት ነው፡፡

የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት፡- ተማሪዎች በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በቃላት አመራረጥ እና አመሰራረት በቃላት አደራደር፣ በቃላት አውዳዊ አገባብ እና በቃላት ፍቺ ምክንያት ያለውን የአረፍተ ነገር መዛባት የሚያመለክት ነው፡፡

የቋንቋ አወቃቀር ስህተት፡- በዚህ ጥናት ውስጥ የቋንቋ አወቃቀር ስህተት ሲባል በአረፍተ ነገር ስምምነት/ባለቤት እና ግስ፣ ጾታ መደብ፣ በቁጥር መዛባት በአያያዦች አጠቃቀም ጉድለት/ የተነሳ የሚከሰቱ የአረፍተ ነገር ቅንብር ወይም ቅደም ተከተል መፋለስ ነው፡፡

የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት፡- በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ በይበልጥ የተለመዱትን የአራት ነጥብ፣ የነጠላ ሰረዝ፣ የጥያቂ ምልክት ወዘተ… በዓረፍተ ነገር ውስጥ በተገቢ ስፍራ አለመዋልን የሚመለከት ነው፡፡

የጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ስህተት፡- የሚያመለክተው የቃሉን ወይም የአገባቡን ምንነት ካመገንዘብ የተነሳ የተለየ ትርጓሜ የሚሰጥበት ሁኔታ መሆኑን ነው፡፡

አማካይ ስህተት፡- በድርሰቶች ውስጥ የተቆጠሩት ስህተቶች ለድርሰቶቹ ጠቅላላ ድምር ተካፍሎ የሚገኘውን ውጤት የሚያሳይ ስሌት ነው፡፡

አማካይ የስህተት ድግግሞሽ፡- በድርሰቶቹ ውስጥ የተቆጠሩት ስህተቶች ለድርሰቶቹ ጠቅላላ ድምር ተካፍሎና በመቶ ተባዝቶ የሚገኘው ውጤት የሚያሳይ ስሌት ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳን

በምዕራፍ ሁለት የክለሳ ድርሳናት ስር የስህተት ምንነት፣የስህተት ትንተና ታሪካዊ ዳራ፣ የስህተት ምንጮች፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎችና የማስተማሪያ ዘዴ ድክመቶች፣ ማህበራዊና ስነ- ልሳናዊ ሁኔታዎች፣ የስህተት ትንተና ዘዴ እና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት የሚሉት ጽንሰ- ሃሳቦችን የሚመለከቱ መረጃዎች የተጠናቀረበት አብይ ምዕራፍ ነው።

## 2.1 የስህተት ምንነት

የአፍ መፍቻም ሆነ ሁለተኛ ቋንቋን ለመልመድ ጥረት ስናደርግ ስህተቶችን እንፈጽማለን፤ ከተፈጸሙት ስህተቶች በመማርም ቋንቋን እንለምዳለን Dulay et.al. (1982: 138)፣ Brown (1994:254-255)።

ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋ ለመልመድ በሚያደርጉት ጥረት የተነሳ የሚፈጽሙት ስህተቶች ላይ አብዛኞቹ ምሁራን የተለያዩ ምርምሮችን አካሂደዋል። ከምሁራኑ የጥናት ውጤትም መረዳት እንደሚቻለው ከስህተት ምንነት አንስቶ እስከ የስህተት አይነቶች እና ምንጮች ድረስ ተቀራራቢ የሆነ አስተያየት እና ብያኔ ሰጥተዋል። አብዛኞቹ መምህራን ስህተት የሚፈጸመው በተማሪዎች ድክመት የሚመጣ እንደሆነ አድርገው የሚገምቱ ሲሆን ይህም ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ ካለማዳመት፣ ለትምህርቱ በክፊል ትኩረት ካለመስጠት፣ ከመምህሩ የትምህርት አሰጣጥ ወይም ደግሞ ተማሪዎች በሚለማመዱበት ጊዜ በቂ ጊዜ ካለመስጠት የተነሳ የተከሰተ ነው የሚሉ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ግድፈትና ስህተት መፈፀምን የትምህርቱ የመጀመሪያ አካል እንደሆነ አድርገው ይወስዱታል። በመሆኑም ስህተት የድክመት ምልክት ተደርጎ መታየት የሚገባው ሳይሆን የተማሪው የቋንቋ ለመዳ ስርዓታዊ እድገትና ተማሪዎቹ ቋንቋውን በሚጠቀሙበት ጊዜ ያለው ሂደት የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች እንደጉድለት በሚቆጥሩና መወገድ ያለባቸው መሆኑንም በሚያምኑት ዘንድ ተማሪዎቹ ስህተት መፈፀማቸው በመምህሩም ሆነ በተማሪዎቹ ዘንድ ዋጋ የሚያሳጣ ተደርጎየሚወሰድ ስለነበር በርካታ ስህተቶችን መፈፀማቸውም ተግሳጽን ያስከትልባቸው ነበር በማለት (Littlewood 1986, 225) ይገልፃሉ።

ሃሰቡ የሚያስረዳው ብዙውን ጊዜ ስህተት ሊመጣ የሚችለው ተማሪዎች ላይ እንደሆነ የተገለፀ ቢሆንም አንዳንዶች ደግሞ ስህተት መስራትን እንደ ትምህርቱ አካል መውሰዳቸውን ነው፡፡

በተጨማሪም Norrish (1990, 1) ተማሪዎቹ ግድፈትን ወይም ስህተትን ላለመፈፀም ይፈራሉ፡፡ የፍርሃታቸው ምንጭም ተማሪዎቹ ግድፈት ወይም ስህተት በሚፈጽሙበት ጊዜ በቋንቋው አፈ ፈት ተማሪዎች፣ በክፍል ጓደኞቻቸውና በመምህራቸውም ዘንድ ይሳቅብናል፣ ይፌዝብናል እና ቂል ያስመስለናል ከሚል ፍርሃት የተነሳ ትምህርቱ በተማሪዎች ላይ ጥላቻ ያሳድርባቸዋል በማለት ገልፀዋል፡፡

ሀሳቡ የሚያስረዳው ለማሪዎች ስህተት ፍርሃት ምንጭ ሊሆን እንደሚችል እና በመምህራቸው ዘንድ ተቀባይነት ያሳጣናል ብለው ከማሰብ ሊመጣ እንደሚችል ነው፡፡

Lindman (1998, 112) እንደሚሉት ስህተት የመማር ሂደት አንዱ አካልና ትምህርቱም በንቃት ለማካሄድ ጠቃሚ ምልክት ነው፡፡ ስህተት ቀደም ሲል በልማዳዊ ሁኔታ በተለያዩ ምክንያቶች (ቃላትን በማጥበቅ፣ በንቃት ባለመከታተል፣ ሃሳበ ብኩን በመሆን ወይም የእውቀት ማነስ…) ተደርጎ ይገለፅ ነበር፡፡ ሆኖም በውጭ ቋንቋዎች ተማሪዎች ላይ ከተካሄደ ምልክታዊ ጥናት የተገኘው መረጃ እንደሚያመላክተው ከታላሚው ቋንቋ አገባብ አለማፈንገጥም ስህተት ላለመፈፀም ዋስትና ሊሆን አይችልም፡፡ ለምሳሌ፡- የጀርመንኛ ቋንቋን የሚማር አንድ ኖርዌያዊ ተማሪ በሰዋስው በኩል ትክክለኛ የሆነ ዓረፍተነገር ሊመሰርት ይችላል፡፡ ነገር ግን ስለፃፈው ጉዳይ እንደገና ዓረፍተነገር እንዲፅፍ ቢጠየቅ የሚሰጠው ምላሽ ከበፊቱ የተለየ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም ሊከሰት የቻለው ሃሳቡን በትክክል ካለመገንዘብ የተነሳ ይሆናል፡፡ በእያንዳንዱ የቋንቋ ተማሪ የሚፈፀሙ ስህተቶችም የተማሪ እድገት አመላካቾች ተደርገው መቀጠር ያለባቸው ናቸው፡፡

እንደ Lindman(1998) እምነት ተማሪዎች በቋንቋው ላይ ላካቸው የአጭርና የረጅም ጊዜ ግብዓትና አጠቃቀም በመነሳት ስለታላሚው ቋንቋ ስርዓት መላምታቸውን እየመሰረቱ ይሄዳሉ፡፡ መምህራን ግን በቋንቋ ለመዳው ሂደት ተማሪዎቹ የሚያመነጪቸውን ነገሮች ዓውድ በማየት ስህተቶቹን ካልገመገሙ በስተቀር በተማሪዎቹ ደረጃ በመምጣትና የተማሪዎቹንም ባህርይ ለማጥናት ሰፊ ምልከታ የሚያካሂዱ እስከሆነ ድረስ ነው፡፡

በሌላ በኩል ሁሉም የሁለተኛ ቋንቋ መምህራን የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት በሚካሄድበት ጊዜ ተማሪዎቻቸው የተለያዩ ስህተቶችን እንደሚፈጽሙ ያውቃሉ፡፡ እነዚህ ስህተቶችም በተማሪዎች

የንግግር ወይም የጽህፈት ቋንቋ ላይ የታየንና ተማሪው በታላሚው ቋንቋ ለመናገር ወይም ለመፃፍ በሚያፈልቅበት ጊዜ ከስነ ድምጽ፣ ሰዋስው፣ ከቃላትና አፃፃፍ ያፈነገጡ ሲሆን ስህተቶቹም ሰዋስዋው፣ አገባባዊ፣ የአፃፃፍና የአጠቃቀም ስህተቶች ናቸው። ስለሆነም አንድ አንባቢ ወይም አድማጭ እነዚህን ስህተቶች የሚገነዘባቸው ከታላሚው ቋንቋ ስነልሳናዊ ህግ የተለያዩ መሆናቸውን ነው በማለት Nagara, E.A. (1983,35) ገልፀዋል።

ከቀረቡት ሃሳቦች መረዳት የተቻለው የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት በሚካሄድበት ጊዜ የሰዋስዋው፣ አገባባዊ፣ የአፃፃፍና የአጠቃቀም ስህተቶች የሚስተዋሉ መሆኑን ነው።

በተጨማሪም Nagara, E.A.(1983, 36) በጥናታቸው መነሻ አድርገው ያቀረቡት ከተፃፉ ድርሰቶች ያገኟቸውን መረጃዎች በመንተራስ ሲሆን አብዛኞቹ ምሳሌዎች የተወሰዱት ከሌስዳና ስዊዝላንድ ዩኒቨርሲቲዎች ነው። ሌሎች ደግሞ ከዝምባቡዌ የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች ጽህፈት ላይ የተወሰዱ ነበሩ። ስለሆነም ጥናቱ ያረፈው የሁለተኛ ቋንቋውን ለረጅም ዓመት የሚያውቁ ተማሪዎች በፈፀሟቸው ስህተቶች ላይ ሲሆን እነዚህ ተማሪዎች ለረጅም ዓመት ለታላሚው ቋንቋ የተጋለጡ በመሆናቸው ለቋንቋው በመጀመሪያ ከተጋለጡት ይልቅ በርካታ ችግሮችን ለመወጣት ይችላሉ የሚል ግምት አላቸው።

በስህተትና ግድፈት መካከል ያለውን ልዩነት በተመለከተ በተለያዩ ዘመናት በተለያዩ ሰዎች ዘንድ የተለያዩ ስያሜዎች ሲሰጡ የቆየ ሲሆን ከእነዚህም መካከል Norrish (1990, 7) ከተለመደው የቋንቋ አጠቃቀም ውጪ ባሉት ባህርያት ማለትም(በስህተት፣ ግድፈትና በንግግር መሃል የሚፈፀም ትንሽ ስህተት) መካከል ያለውን ልዩነት መለየቱ ጠቀሜታ እንዳለው ያስገነዝባሉ። ስህተት ከተለመደው የቋንቋ አጠቃቀም ውጪ ስርዓታዊ በሆነ ሁኔታ ማፈንገጥ ማለት ሲሆን ይህም ተማሪው አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ያልሆነን ነገር በመማሩ የሚፈፀም ነው።

አንዳንድ ጊዜ ተማሪው አንድን የቋንቋ ቅርፅ ይማራል፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ ተመሳሳይ ባልሆነ ሁኔታ ሌላ ቅርፅ ይማራል፤ በመሆኑም በዚህ ወጥ ባልሆነ ሁኔታ መማሩ መሳሳትን ያስከትላል። ይህ መሳሳት ደግሞ ግድፈት ይባላል። ግድፈት ሲባልም ተማሪው አንዳንድ ጊዜ ነገሩን በትክክል ሲያገኘው ሌላ ጊዜ ደግሞ ስህተት በመፈፀም በተሳሳተ ቅርፅ ይገለገልበታል።

በማንኛውም ጊዜ በማንኛውም ሁኔታ ግድፈትም ያልሆነ ስህተትም ያልሆነ የቋንቋ አጠቃቀም ይከሰታል። ስህተቱም በትኩረት ማነስ፣ በዝንጋታ፣ በስራ ምክንያት፣ ከሰውነት መዛልና

መድከም የተነሳ የሚከሰት ነው። ይህም ቋንቋውን ይማሩትም አይማሩትም ወይም ደግሞ ሁለተኛ ቋንቋውን በሚማሩበት ጊዜ የተሰጠ የቋንቋው ቅርፅ ይሁንም አይሁንም ሊከሰት የሚችል ነው።

ከሃሳቡ መረዳት የሚቻለው ግድፈት የምንለው ወጥ ባልሆነ ሁኔታ ከሚማረው የቋንቋ ቅርፅ የሚከሰት ሲሆን ስህተት የሚባለው ደግሞ በቀጥታ ከተማሪው ማንነት ጋር ማለትም ትኩረትና መሰል ነገሮች ጋር የሚገናኝ መሆኑን ነው።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁኔታም Morrissey (1983, 196) የተለያዩ ምሁራንን ሃሳብ ወስደው እንደሚሉት ግድፈት በአፍ መፍቻ ቋንቋና በሁለተኛ ቋንቋ መማር ላይ የሚከሰት ሲሆን ይህም ስህተት ፈፃሚው ስህተቱን አውቆ በቀላሉ ሊያርመው የሚችለው ዓይነትና ኢ- ስርዓታዊ ስህተት ወይም የቋንቋ ብቃት ስህተት በመባል የሚታወቀው ነው። ስህተት ስርዓታዊ ስህተት ወይም የቋንቋ ችሎታ ስህተት በመባል የሚታወቅ ሲሆን ህም በቋንቋ ለመዳ ወቅት ሊከሰት የሚገባ ነው።

ግድፈት ስህተት ፈፃሚው አካል ራሱን ማረም ወይም ማስተካከል የሚችልበት ሁኔታ እንዳለ የሚያስረዳ ሲሆን ስግተት ግን በቋንቋ የችሎታ ልክ ሊፈጠር እንደሚችል አማሳየቱም ባለፈ ስህተት የሌሎችን ሰዎች ወይም የመምህራንን እገዛ ሁሉ ሊጠይቅ እንደሚችል መረዳት የሚያስችል ነው።

Nagara, E.A. (1983, 6) ከ Morrissey ሃሳብ ባልተለየ ሁኔታ የግድፈትንና ስህተትን ልዩነት ይገልፁታል። እንደ እርሳቸው አስተሳሰብም የቋንቋ ብቃት ስህተት የሚፈፀመው ተማሪው ቋንቋውን ባለማወቁ ሳይሆን በሚናገርበት ወይም በሚጽፍበት ጊዜ በነበረ ጭንቀት፣ ጫና፣ መርሳት ወይም ግድየለሽነት የተነሳ ሲሆን፣ የስህተቶች መከሰት ግን ተማሪው ታላሚውን ቋንቋ የማወቁን የደረጃ መጠን የግድ አያንጸባርቅም። የቋንቋ ችሎታ ስህተቶች የሚባሉት ግን ተማሪው ታላሚውን ቋንቋ በሚጠቀምበት ጊዜ ያለውን የቋንቋ ችሎታ ውስንነት የሚያንጸባርቁ ናቸው።

ካቀረብኳቸው የምሁራን ሃሳቦች መረዳት የተቻለው ግድፈት ወይም የቋንቋ ብቃት ስህተት በቀላሉ የሚታረም መሆኑን ሲሆን ስህተት ወይም የቋንቋ ችሎታ ስህተት ደግሞ የታላሚው ቋንቋ ላይ የችሎታ ውስንነት ሲስተዋልበት መሆኑን መገንዘብ የተቻለ ሆኗል።

Brown (1994, 254- 205) ከ Morrissey እና Nagara, E.A.ሃሳብ ጋር በሚቀራረብ መልኩ የሰውን ልጅ ቋንቋ የመማር ሂደት ከዋና ሂደት ጋር በማመሳሰል ገልፀውታል፡፡ህጻናት የአፍ መፍቻ ቋንቋውን ሲለምዱ ስህተቶችን ሲፈጽሙ በሌሎች ሰዎች ከሚሰጣቸው መረጃ ምገባ በመነሳት በጥንቃቄ ግን በዝግታ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተቀባይነት ያለውን ንግግር ያፈልቃሉ፡፡ ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ሂደትም ካለው የስህተት መማር ባህሪው በግልጽ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ የተለየ አይደለም፡፡ የማይቀረው ነገር ቢኖር ግን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በቋንቋ ለመዳ ሂደት ስህተት መፈጸማቸው ሲሆን፣ ስህተት የማይፈጽሙ ከሆነና ከፈጸሙት ስህተት በመነሳት ከሌሎች ሰዎች በተሰጣቸው የማስተካከያ ሃሳብ ማረም ካልቻሉ ግን የቋንቋ ለመዳ ሂደት ሊደናቀፍ ይችላል፡፡

በጥቅሉ ስህተቶች የቋንቋ ችሎታ ነፀብራቆች ሲሆኑ እነሱም ተማሪው በታላሚው ቋንቋ በሚገባ ያላወቃቸው አካባቢዎች የትኞቹ እንደሆኑ የሚያመላክቱ፣ የተማሪውንም ሆነ የአስተማሪውን ስራ በይበልጥ የሚጠይቁ፣ ቋንቋን እንዴት መማር ወይም መልመድ እንደሚቻል፣ ተማሪው ቋንቋውን ለማሻሻል ምን ዓይነት ስልትና ስልተ- ትግበራ ሊከተል እንደሚገባው ለተማሪው ማረጋገጫ የሚሰጡ ናቸው በማለት Morrissey (19876፣ 196) ፣Nagara, E.A. (1983፣6) እና Brown (1994፣ 204- 205) መግለጽ ችለዋል፡፡

ሃሳቡ የሚያስረዳው ስህተቶች የቋንቋ ችሎታ ነፀብራቆች በመሆናቸው የአስተማሪውን ስራ የሚጠይቁ መሆናቸውን የሚያስገነዝብ ነው፡፡

በሌላ አገላለጽ ስህተት ተማሪው በትክክለኛው ስርዓት የማይጠቀም ከሆነ እንደገና በመድገም ከትክክለኛው የቋንቋ አጠቃቀም ስርዓት የሚደርሰው ነው በማለት Spolisky (1979፣ 250) ገልጸዋል፡፡

በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ሂደት የሚከሰቱት የእነዚህ ስህተቶች ምንነትና ጠቀሜታ የተገለጸ ቢሆንም ለስህተቱ መፈጸም አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የተለያዩ የስህተት ምንጮችም እንዳሉ በተለያዩ ምሁራን ዘንድ በተለያዩ መልኮች ተጠቅሰዋል፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት ተከታይ ክፍል ለስህተት ምንጭ ይሆናሉ ተብለው የሚታሰቡት እንደሚከተለው ማቅረብ ተችሏል፡፡

## 2.2 የስህተት ትንተና ታሪካዊ ዳራ

የስህተት ትንተና የተማሪዎችን ስህተት መሰረት አድርጎ ስህተትን ግልጽ በሆነ ዓላማ፣ አመቺና ውጤታማ በሆነ መንገድ የመተንተን ሂደት ነው፡፡ የስህተት ትንተና የስህተት አይነቶችን እና ምንጫቸውን ለመተንተን የምንጠቀምበትና ሰፊ ተቀባይነት እያገኘ የመጣ የጥናት መስክ ነው በማለት Ellis (1989,5) እና Sharma (1986,76) አብራርተዋል፡፡

ሃሳቡ የሚያስረዳው የስህተት ትንተና ዘላቂ በሆነ መንገድና ግልፅነት ባለው ዓላማ ተመስርቶ ውጤትን ሊያመጣ በሚችል መልኩ የተሰሩትን ስህተቶች ዘርዝሮ በማቅረብ፣ የስህተቶች መከሰቻ ምንጮችን የመለየት መንገድ እንደሆነ የሚያትት መሰረታዊ ሃሳብ መሆኑን መረዳት የሚያስችል ነው፡፡

ይህ የጥናት ዘርፍ ተጅም ጊዜ ያስቆጠረ ሲሆን አስፈላጊነቱ እየታወቀ የመጣውም በ1950ዎቹ መጨረሻ ላይ እና በ1960ዎቹ መጀመሪያ ላይ ነበር፡፡ በዚህ ዘመን የስህተት ትንተና በንፅፅራዊ ትንተና ሊገለፅ ያልቻለውን የተማሪዎችን ስህተት በመተንተን ላይ ያተኮረ አካሔድ ነበረው የስህተት ትንተና እያደገ ከመምጣቱ አስቀድሞ የተማሪዎችን ስህተት በመተንተን ገናና የነበረው ንጽጽራዊ ትንተና ሲሆን ይህም የባህሮታውያንን ስነልቦና (Behavioral Psychology) የተከተለ የጥናት መስክ ነበር፡፡ የባህሮታውያን ስነልቦና አራማጆች ትምህርት የልምድ ክምችት ነው ተብሎ ስለሚታመን ተማሪዎች ስህተትን የሚፈጽሙት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ልምድ የተነሳ አዲሱ የቋንቋ ለመዳ መሰናክል ስለሚያጋጥመው እንደሆነ ይታሰባል በማለት Dulay et al (1982, 140-141) ገልፀዋል፡፡

ሃሳቡ የንጽጽር ትንተና ከስህተት ትንተና የቀደመ፣ በሰፊው ይሰራበት የነበረና የስነልቦና አስተሳሰቦች ላይ የሚያተኩር መሆኑን መገንዘብ የተቻለበት ጽንሰ- ሃሳብ ነው፡፡

ስለዚህ ንጽጽራዊ ትንተና የተማሪውን የአፍ መፍቻ ቋንቋ እና የታላሚውን ቋንቋ መሰረት አድርጎ ስህተትን ይተነትናል፡፡ በዚህ የጥናት መስክ እምነት የስህተት ምንጭ የተማሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ውስጥ ጣልቃ መግባት ነው፡፡ አሮጌው ልምድ ማለትም ተማሪው አፍ የፈታበት ቋንቋ በአዲሱ ልምድ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ ህፃንም ሆነ አዋቂ ሁለተኛ ቋንቋቸውን በሚማሩበት ጊዜ ስህተትን ቢሰሩ፣ የሰሩት ስህተት ምክንያት አፍ የፈቱበት ቋንቋ ተጽዕኖ ነው ተብሎ ስለሚታመን ስህተትን በመተንተን የሁለቱን ቋንቋዎች ስነልሳናዊ ባህርያት መሰረት በማድረግ እንደሚገባ ይሰመርበታል፡፡ ይህም ለአፍ መፍቻ ቋንቋ

አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖር አድርጓል በማለት Richards and Sampson (1974, 5), Dulay et al (1982, 5) Ellis (1989, 295) Rivers and Temperley (1978, 151), James (1996,20) አብራርተዋል፡፡

ሃሰቡ የስህተት ትንተና ባልተንሰራራበት ዘመን በተማሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋና በታላሚው ቋንቋ መካከል የሚኖርን ስህተት ይተነትን እንደነበር ሲያሳይ ማንኛውም ሁለተኛ ቋንቋውን የሚለምድ አካል ስህተት እንደሚሰሩ በማመን የቋንቋዎችን ባህርያት መሰረት በማድረግ ስህተቶችን ማየት እንደሚገባ ያሳያል፡፡

ይሁን እንጂ በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የስህተት ምንጭ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ ብቻ አይደለም፡፡ ሌሎችም የስህተት ምክንያቶች አሉ፡፡ እንዲያውም በብዙ ምሁራን እንደሚገለጸው  የሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ራሱን የቻለ የፈጠራ ሂደት ስላለው በዚያ የሂደት ውስጥ ተማሪዎች በሚፈጥሩት መላምት የተነሳ የፈጠራ ስህተት ስላለ የአፍ መፍቻ ቋንቋውን ብቻ የስህተት ምጭ ማድረግ ተገቢ እንዳልሆነ ይታመናል፡፡ ንጽጽራዊ ትንተና የሚተችበት ሌላው መንገድ ስህተቶችን በንጽጽራዊ ዳታ ከማሳየት ውጪ ተጨማሪ ነገር አለመስጠቱ ነው፡፡ ምንም እንኳን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ የሚመጡ ስህተቶችን ለይቶ ለማሳየት ጠንካራ ጎን ቢኖረውም ከመለየት ውጪ ምንም አለመፈፀሙ ግን ድክመቱን ያጎላዋል Rivers and Temperley (1978, 151), Richards and Sampson (1979, 5), Dulay et al (1982,5), Ellis (1989,259) አብራርተዋል፡፡ ይህም በመሆኑ ሌላ የጥናት መስክ ሊጀመር የግድ ሆኗል፡፡

Corder (1974) የስህተት ምንጭ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ብቻ እንዳልሆነ በመገለጹ የተነሳ የስህተት ትንተና እንደገና ሊያንሰራራ በቅቷል ይላሉ፡፡ ከ Corder በኋላም የተለያዩ ምሁራን የተማሪዎችን የድርሰትና ንግግር በመተንተን የስህተት ምንጮችን መተንበይ ጀመሩ፡፡ በዚህም የተነሳ አብዛኞቹ በተማሪዎች የሚፈፀሙ ስህተቶች ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ውጪ እንደሆኑ ሊረጋገጥ ተችሏል፡፡

የስህተት ትንተና ስህተትን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ከፋፍሎ በማጥናት ምንጮቹን መጠቆሙ አንዱ ጠቃሚ ጎኑ ነው፡፡ በተጨማሪም ለስህተት ያለውን አሉታዊ አመለካከት ወደጎን በመተው ስህተትን እንደአንድ ጠቃሚ የትምህርት ሂደት በመመልከት ለስርዓተ ትምህርት ቀረፃ፣

ለማሪያ መፃህፍት ዝግጅት እንዲሁም ተማሪዎች ያሉበትን ደረጃ ለመለኪያነት የሚያገለግል ሆኗል፡፡

የስህተት ትንተና የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም በናሙናነት በመሰብሰብ ስህተቶችን ለይቶ ያወጣል፡፡ከዚህም የስህተቶችንምንነት በመግለፅ ምንጫቸው ምን ሊሆን እንደሚችል መላምት ይመታል፡፡ አያይዞም የስህተቶቹን የክብደት ደረጃ ይለያል፡፡ በዚህ መሰረት Richards (1979) እንግሊዘኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ አፋቸውን በተለያዩ ቋንቋዎች የፈቱ ተማሪዎችን ስህተት ወስደው በማጥናት በሁለቱም ላይ የተንፀባረቁ አራት የስህተት ዓይነቶችን መለየት ችለዋል፡፡ ማጠቃለያቸውም የታላሚውን ቋንቋ ህግ አለማወቅ፣ ህጉን ባልተሟላ ሁኔታ መተግበር እና የተሳሳተ ዘዴ ወይም ፅንሰ ሃሳብ ሲሆን ስህተቶቹም ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ ውጪ የተፈጠሩ ናቸው Dulay et al (1982, 138- 141), በማለት ገልፀዋል፡፡

የቀረበው ሃሳብ የሚያስገነዝበው የስህተት ትንተና አንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚነገሩ ሁለት ቋንቋዎችን በመውሰድ ተማሪዎች ላይ የሚስተዋሉትን ስህተቶችና የሚያሳድሩባቸውን ተፅዕኖዎች በመለየት እንዲሁም የክብደት ደረጃቸውን ማወቅ እና መፍትሄዎችን ማስቀመጥ መቻል እንደሆነ መረዳት ተችሏል፡፡

Ellis (1989, 296) እና Corder (1974, 19) በእርግጥ ተማሪዎች ስህተቶችን ይፈጽማሉ፡፡ እነዚህ ስህተቶችም ምልከታ ሊደረግባቸው፣ ሊተነተኑ እና በየክፍላቸው ሊሰደሩ ይገባል፡፡ ይህ የተማሪዎች የስህተት ጥናትም የስህተት ትንተና የሚል ስያሜተሰጥቶታል፡፡

ስህተቶች እንኳን በተማሪዎች በማንኛውም የሰው ልጅ የሚከሰት መሆኑ የሚዘነጋ ባይሆንም ተማሪዎች  ድርሰቶችን ሲጽፉ በርካታ ስህተቶችን እንደሚሰሩ ከምሁሩ ገለፃ መረዳት ችያለሁ፡፡

በተያያዘ ገለፃም የስህተት ትንተና ለተማሪዎች የስህተት ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉትን ነገሮች ለመለየት ሁሉንም አማራጮች ይጠቀማል Brown (1994፣ 206) በሚል ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ የስህተት ትንተና ከድክመት የፀዳ ነው ለማለት አንችልም፡፡ ከእነዚህም ምክንያቶች አንዱ ለአንድ ስህተት መፈፀም ከአንድ በላይ የሆኑ ምክንያቶች ሊኖሩ ቢችሉም ትንተናው በአንዱ ውስጥ ሲያካትተው ሌሎቹ ምንጮች ችላ ሊባሉ መቻላቸው ነው፡፡

ሌላው በንጽጽራዊ ትንተና አቀንቃኞች የሚነሳ ሲሆን አንድን ስህተት ሁለንተናዊ ነው ማለት ወይም ደግሞ ከታላሚው ቋንቋ ተፅዕኖ የተነሳ የተፈጠረ ነው ብሎ ለመፈረጅ የስህተት ትንተና

የሚከተለው በተለያዩ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የጋራ ስህተት የመቀነስ አቅጣጫ በአፍ መፍቻ ተፅዕኖ ሳለመፈጠሩ ዋስትና ስለማይሆን የግድ የጎን ለጎን የተማሪዎች አፍ መፍቻ ቋንቋ መጠናት አለበት መባሉ ነው Dulay et al, (1982, 192), Jemes (1996, 186-187)።

ከሃሳቡ መረዳት የሚቻለው በተለያዩ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የጋራ ስህተቶችን ለመቀነስ የሚያደርጉጥ ጥረት አፋቸውን የፈቱባቸው ቋንቋዎች ላይ ተፅዕኖ ሊፈጠር ስለሚችል የአፍ መፍቻ ቋንቋዎቻቸው መጠናትና ጎን ለጎን መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል።

Lott (1983, 256- 257) በስህተት ትንተና ላይ የሚታዩ ድክመቶች በተጠኝዎቹ ቋንቋዎች ተቀራራቢነት፣ አጥኚው ይዞት በሚነሳው ርዕሰ ጉዳይ ስፋትና ጥበት፣ በአጠናን ዘዴውና ከተጠኝዎች ሁኔታ አንፃር የሚፈጠሩ ናቸው። በዚህም የተነሳ በአንድ ዓይነት ቋንቋ ላይ የሚሰሩ ጥናቶች እንኳን በጣም የተለያዩና አንዳንዴም ተቃራኒ ውጤቶችን ሲያስመዘግቡ ይጠቀሳሉ።

ከምሁሩ አገላለፅ መረዳት የተቻለው በስህተት ትንተና ላይ የሚስተዋሉት የድክመት ጎኖች በአጥኚው፣ በተጠኝዎች፣ በጥናቱ ርዕስ፣ በጥናቱ ዘዴ እና በጥናቶች ውጤትም ጭምር ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል እንደሆነ መቅሰም ተችሏል።

እንደ Dulay et al (1982, 141- 146) ገለፃ የስህተት ትንተና ቢያንስ ሶስት መሰረታዊ ድክመቶች አለበት። እነዚህ ድክመቶችም ሊሰጥ የሚችለውን ጠቀሜታ ያህል እንዳይሰጥ አግደውታል። ድክመቶቹም አንደኛ በስህተት ትንተናው ሂደት ላይ ስህተቶችን እንዲህ ናቸው ብሎ በግልጽ ለመናገር አለመቻልን ምንጫቸውንም በተገቢ ሁኔታ ማስፈር አለመቻል፣ ሁለተኛው የስህተት ክፍሎችን ግልጽ በሆነ ሁኔታአለማስፈሩ፣ ሶስተኛ የተማሪዎችን ስህተቶች ቀላል በሆነ መንገድ መከፋፈል አለመቻል ናቸው። ይሁን እንጂ ይህ የጥናት መስክ ድክመቶችን እያረመ በመምጣት ላይ በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ ሰፊ ተቀባይነትም እያገኘ ከመምጣቱ ባሻገር በማህበራዊ ስነልሳን እና በቋንቋ ትምህርት ዘርፎች ትልቅ አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ እንደሆነ የዘርፉ ምሁራን ይስማሙበታል።

ከሃሳቡ መረዳት የቻልኩት የስህተት ትንተና ማስገኘት ያለበትን ያህል ጥቅም እንዳያስገኝ የሚያደርጉ፣ ስህተቶችን በሚገባና ግልጽነት ባለው ሁኔታ መድቦ የማያቀርብ መሆኑና

ስህተቶችን ተማሪዎች ራሳቸው ከፋፍለው ማቅረብ አለመቻላቸው የሚሉት ከክፍተቶቹ መካከል የሚጠቀሱ መሆኑን ነው፡፡

## 2.3 የስህተት ምንጮች

ስህተቶች በተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ የሚፈጠሩ የራሳቸውም መከሰቻና መንስኤ ያላቸው ክንዋኔዎች ናቸው፡፡ ጽህፈትም ተግባር እንደመሆኑ በዚህ ተግባር ልምምድ ላይ የሚከሰቱ ስህተቶች ይኖሩታል፡፡

በስህተት ትንተና ጥናት ውስጥ የተማሪዎች ስህተት የሚመነጨው ከተለያዩ ምክኒያቶች ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ያም በመሆኑ እንደሚጠኑት ቋንቋዎችና ተማሪዎች እንዲሁም እንደ አጥኚዎች አተያይ የስህተት ምንጮች በተለያዩ ክፍሎች ተመድበው ይቀርባሉ፡፡ በመሆኑም ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች ለሚፈፅሟቸው ስህተቶች ምንጭ ይሆናሉ ተብለው የሚገመቱ አያሌ ምክኒያቶች መኖራቸውን ማንጠግቦሽ (2009) ትገልፃለች፡፡

ቋንቋን በመማር ወይም በመልመድ ሂደት የሚስተዋሉት የስህተቶች ምንጭ የውጫዊና ውስጣዊ ተፅዕኖዎች ድምር ውጤት እንደሆነ Dulay et.al(1982:144) ይጠቁማል፡፡ በመሆኑም የቋንቋ መምህሩ የስልጠና ሂደቶች፣ የተማሪው ባህላዊ አውዶች እና ለቋንቋ የሚኖረው ተጋልጦ እና የመሳስሉት ውጫዊ እና እንዲሁም የአፍ መፍቻ ቋንቋ አሉታዊ ሽግግር የሁለተኛ ቋንቋን ህግጋት በተግባቦት ሂደት ለመተግበት ሲሞከር የሚጠቀምባቸው የተሳሳቱ መላምቶች ከተማሪው ሰነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች ጋር የተያያዙ ውስጣዊ ጉዳዮች የተናጠልም ሆነ የጋራ ድምር ውጤት ናቸው፡፡

ምሁራን እንደሚገልፁት የስህተት ምንጮች የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በአንድ በኩል በርካታ ስህተቶች ከአንድ የስህተት ምንጭ ሊመጡ እነደሚችሉና በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ስህተት የበርካታ የስህተት ምንጮች ውጤት ሊሆን ይችላል፣ በመሆኑም ስህተቶችን ከምንጫቸው አኳያ ለመመደብ ሙከራ የሚያደርግ ተመራማሪ አስቸጋሪና ዘፈቀዳዊ ውሳኔዎችን የማሳለፍ እድል እንደሚገጥመው ምሁራኑ ጨምረው ይገልፃሉ፡፡

በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ሂደት በሚፈጠር ስህተት ላይ ሁለት መሰረታዊ ልዩነት ያላቸው አመለካከቶች አሉ፡፡ የእነዚህ አመለካከቶች ልዩነት የሚነሳውም በስህተት ምንጩ ወይም ስህተት እንዴት ሊከሰት ይችላል በሚለው እሳቤ ላይ የተለያዩ አመለካከቶች በመንፀባረቁ ነው፡፡

የልዩነት መከሰቻ የስህተት ምንጭ ናቸው ተብለው የሚታመኑት ወይም ተማሪው ስህተትን ለምን ይሰራል? ለሚለው ጥያቄ የሚሰጠው ምላሽ መለያየት ነው፡፡

የመጀመሪያው አመለካከትተገቢና ፍፁም በሆነ የማስተማር ዘዴ ከተማረ ስህተት ሊከሰት አይችልም ብሎ ከማመን የመነጨ ነው፡፡ ስለዚህም የስህተት መከሰቻው ወይም መገኛው ተገቢ ወይም ፍፁም የሆነ የማስተማር ዘዴ አለመኖር ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህም መምህሩ ትምህርቱን በተገቢ መንገድ ለተማሪዎች ግልፅ ባለማድረጉ የሚከሰት ነው ከሚል እሳቤ ይመነጫል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተማሪው ለትምህርቱ ተገቢውን ትኩረት ባለመስጠቱ ወይም በተገቢው መንገድ ባለመማሩ የተነሳ የተከሰተ ውድቀት ነው ተብሎ ይታመናል Corder (1979, 120) በማለት አብራርተዋል፡፡

የቀረበው ሃሳብ ውስጥ መረዳት የተቻለው የማስተማሪያ ዘዴው ፍፁም ከሆነ ስህተት እንደማከሰት ጠሚያስረዳ ነው፡፡

እንደ Norrish (1992, 1 -2)ገለፃ በብዙ ባህላዊ የቋንቋ ትምህርቶች ተማሪዎች ስህተትን እንዲሰሩ አያበረታቱም፡፡ ስህተት መወገድ ያለበት ጉዳይ እንደሆነ ስለሚታመን፣ በመደበኛ ክፍል ውስጥ ስህተት መፈፀም ተገቢ እንዳልሆነ ይታመናል፡፡ ይህም በመሆኑ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በመምህራቸው ወይም በአፊ ፊት ተማሪዎች እንዳይተቹ ሲሉ ስህተት መፈፀምን አጥብቀው ይፈራሉ፡፡ ስለሆነም የተማሪው ጭንቀት መግለፅ የተፈለገውን ጉዳይ እንዴት መናገር ወይም መፃፍ እንዳለበት ማሰብ ሳይሆን ያለ ስህተት እንዴት መናገር ወይም መፃፍ እንደሚችል ነው፡፡ ይህም መልዕክት ማስተላለፍ ሁለተና ቦታ እንደሚሰጠው  እና ትክክለኛውን ቅርፅ መናገር ወይም መፃፍ ደግሞ ቀዳሚ እንዲሆን የሚያደርግ ነው፡፡

በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ሂደት የሚፈጠርን ስህተት አስመልክቶ ያለው ሁለተኛው አመለካከት ፍፁም ባልሆነ ምድር ላይ የምንኖር እንደመሆናችን መጠን፣ ፍፁም የሆነ ቋንቋን የማስተማሪያ ዘዴ ልናገኝ አንችልም፤ በመሆኑም ተማሪዎቻችን ስህተትን መፈፀማቸው አይቀሬ ነው የሚል መነሻ ሀሳብ የያዘ ነው፡፡ ይህ አመለካከት የሚያነሳው ሌላው ነጥብ የቋንቋን ግብዓትና ውጤትን መሰረት ያደረገ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ብዙዎቻችን ሁለተኛ ቋንቋን ስንማር በቂ እውቀት ይኖረንና በሚገባ ማዳመጥና ማንበብ እንችላለን፡፡ ይሁን እንጂ በቋንቋው ራሳችንን ለመግለፅ በምንሞክርበት ጊዜ ብዙ ስህተቶችን እንፈፅማለን፡፡ ይህም ተፈጥሯዊ የሆነ የቋንቋ ለመዳ

ስለሆነ መበረታታት አለበት እንጂ መሰናቀፍ የለበትም የሚለው አመለካከት በዚህ እምነት አራማጆች ይታመናል በማለት Corder (1979, 20), Norrish (1992, 3) አብራርተዋል።

ከላይ የቀረቡት የምሁራን ሃሳቦች እርስ በርስ የሚጣረሱ ሆነው ቀርበዋል። ማለትም የመጀመሪያው ማስተማሪያ ዘዴው ፍፁም ሲሆን ስህተት እንደማይከሰት የሚያስረዳ ሲሆን ሁለተኛው አገላለፅ ደግሞ ፍፁም የሆነ የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ወይም ፍፁም በሆነ መንገድ ትምህርቱን ማቅረብ እንደማይቻል ነው።

ብዙ ምሁራን እንደሚታመነው ስህተት መሰረታዊ የሆነ የቋንቋ ትምህርት አካል ነው። ህፃናት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ሲማሩ ስህተት ሊፈፅ ይችላሉ። ይሁን እንጂ በወላጆቻቸውና በዙሪያቸው ባሉ ሰዎች በሚደረግላቸው ያላቋረጠ እርማት ማህበረሰቡ ትክክል ነው ብሎ ወደተቀበለው አጠቃቀም ይመጣል። እንደዚሁም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትም ስህተት እንደ አንድ የማስተማሪያ ዘዴ እና አይቀሬ እንደሆነ የትምህርት አካል ሊታይ ይገባል። ሁሉም የሁለተኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎቻቸው ስህተትን እንደሚፈፅሙ ያውቃሉ። የእነዚህ ስህተቶች ዓይነትና ምንጮችም የተለያየ ሊሆን ስለሚችል የስህተቱን ምንጭ አውቆ ተማሪዎች ከስህተታቸው እንዲታረሙ ማድረጉ ተገቢ እንደሆነ በብዙ ምሁራን ይታመናል Corder (1974, 20), Norrish (1992, 6-7) በማለት ገልፀዋል።

### 2.2.1 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ

Norrish (1992) ሲገልፁ ቋንቋን የመማር ሂደት የተሞክሮ ወይም የልምድ ስብስብ ውጤት ስለሆነ የተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ልምድ ጣልቃ በመግባት ስህተት ምንጭ ሊሆን ይችላል።አዲስ ቋንቋ በምንለምድበት ጊዜ አዲስ ልምድ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር ሲሆን በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያሉ የድምፅ በሌላ ውስጥ ላናገኛቸው ይችላል። ያን ቋንቋ በምንማርበት ወይም በምለምድበት ጊዜ ስነ ድምፃዊ ችግር ሊያስከትል ይችላል። በመሆኑም በሁለተኛ ቋንቋ ለሚማረው ተማሪ አፉን የፈታበት ቋንቋ መዋቅራዊ ተፅዕኖ ሊያደርስበት የሚችል ነው።

በአጠቃላይ ከእነዚህ እውነቶች መረዳት የሚቻለው ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ ከዋነኞቹ የስህተት ምንጮች እንደ አንዱ ሊቆጠር እንደሚገባ ነው።

አንድን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በሚሰጠው ቋንቋ በሚማሩበት ወቅት ከመጀመሪያው ደረጃ ላይ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች መንስዔዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ እንደሆነ በርካታ ምሁራን ሀሳባቸውን ይሰጣሉ። በመሆኑም አፍ መፍቻው በሁለተኛ ቋንቋ

አጠቃቀም ስርዓት ከመልመዳቸው አስቀድሞ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ብቸኛ ልምዳቸው ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች አፍ የፈቱበትን ቋንቋ ሀሳብ እንዲወስዱ በታላሚው ቋንቋ የሚጠቀሙት ስለሆነ በሚጠቀሙበት ወቅት ተጽዕኖው አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን ይችላል፡፡ አዎንታዊ የምንለው የታላሚው ቋንቋና ተማሪው አፍ የፈታበትና ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ መዋቅራዊ ስርዓት ያለው ይሆንና ተማሪው አፉን የፈታበት ቋንቋ መዋቅራዊ ስርዓት ያፈነገጠ ስለሚሆን ለስህተት ተጋላጭ ይሆናል በማለት Norrish (1992) አብራርተዋል፡፡

## 2.3.2 የውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ

ሌላው የስህተት ምንጭ ነው ተብሎ የሚታወቀው አሉታዊ ውስጠ ቋንቋ ሽግግር ስህተት የሚባለው ሲሆን ይህም አንድ ጊዜ ተማሪው የሁለተኛ ቋንቋውን አዲስ ስርዓት ከለመደ በኋላ የታላሚውን ቋንቋ ሽግግር በይበልጥ እየጨመረ ለመሄድ ስህተት የሚያመጣ ነው፡፡ Brown (1994,214) እና Littlewood (1986,23)ገልፀዋል፡፡

ይህንኑ በተመለከተ Nagara (1983, 36)ለውስጠ ቋንቋ ስህተቶች መፈጠር ምክንያት የሆነውን ጉዳይ በርካታ ምሁራን የስህተት ብያኔ ብለው እንደሚጠሩት ከገለፁ በኋላ ለውስጠ ቋንቋ መነሻ የሆኑትን ሶስት ጠቃሚ ጉዳዮች ተመራምረው በማግኘት እነዚህ ምክንያቶችም ያልተሟላ ትምህርት፣ የተሳሳተ ቅንጅትና ያላግባብ ቃላትን መጠቀም ናቸው በማለት ይገልጿቸዋል፡፡

የስህተት ብያኔ ማለት ተማሪው በታላሚው ቋንቋ ያወቃቸውን የቋንቋውን ህጎች ወይም ስነ ልሳን ጊዳዮች በማይመለከተው ስፍራ ወይም ተገቢ ባልሆነ አውድ ተግባራዊ ማድረግ እንደሆነ ከጠቆሙ በኋላ ይህም በቋንቋው ውስት ያለውን አጠቃላ ህግ በማስፋፋት የመጠቆም ጎዳይ እንደሆነ Nagara (1983) ልፀውታል፡፡

እንደ ምሁሩ አስተያየት በውስጠ ቋንቋ ስህተቶች ምክንያት ይሆናል ተብሎ የተገመተው ያልተሟላ የትምህርት ስህተት የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪው ከታላሚው ቋንቋ መዋቅር፣ ከቃላቱ፣ ከአገላለፁ ወይም ደግሞ ሌላ ገፅታ ውስጥ ግማሹን ብቻ የተማረ መሆኑና ሊያፈለክቅ የሚችለውም ከመዋቅሩ፣ አገላለፁ… በከፊል በመሆኑ ከፊሉ ብቻ ትክክል ይሆናል፡፡ በዚህም ምክንያት ያልተሟላ ትምህርት ለስህተት መነሻ ይሆናል፡፡

ያልተሟላ ትምህርት ስህተት የሚባለው ተለያዩ ዘርፎች ያሉት ሲሆን እነዚህም፡-

- ✓ ያልተሟላ የሰዋሰው ህግ፣

- ✓ ያልተሟላ የመስተዋድዳዊ ሃረግ ትምህርት፣
- ✓ ያልተሟላ የቋንቋ አገላለፅ ትምህርት እና
- ✓ ፍችን (ትርጉምን) በቀላሉ ለመለየት ወይም ለመገንዘብ ያልተቻሉ የቃላት አይነት ናቸው፡፡

ትክክል ያልሆነ ዝምድና የሚከሰተው ተማሪው በታላሚው ቋንቋ የተማሪው ስነልሳናዊ ቅርፅ በዚያው ቋንቋ ካለ ሌላ ቅርፅ ጋር በሚጋጭበት ጊዜና በመጠቀም ከተለመደው የቋንቋ ስርዓት ውጪ ያፈነገጠ ቅርፅ በሚመነጭበት ጊዜ ነው፡፡ ትክክለኛውን የቋንቋ ቅርፅ ትክክል ካልሆነ ጋር የማዋሃዱ (የማዛመዱ) ጉዳይም ስነ- ምዕላዳዊ፣ ፍችያዊ ወይም ደግሞ ሰዋሰዋዊ ሊሆን ይችላል፡፡ "ያለአግባብ ቃላትን መጠቀም" የሚባለውም መለያ ባህሪው ከፍተኛ ድምፅ ባላቸው ቃላትና በረጃጅም ዓረፍተነገሮች ሲሆን ተናጋሪው ወይም ፀሃፊው በታላሚው ቋንቋ ያለውን እውቀት ለማመልከት በሚጨነቅበት ጊዜና በአድማጭ ወይም አንባቢው ትኩረት ለመስጠት ሲፈልግ የሚከሰት መሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ሁኔታ ሃሳቡን ከመግለፅ ሲፈለግ የተሳሳተ የቃላት አጠቃቀም፣ ትርጉም አልባ አገላለፅና የቃላት ግንባታ ሲከሰት ትርጉም የለሽ ቃላትን መደርደሩም ያለአግባብ ቃላትን መጠቀም የተለመደ ገፅታ ነው Nagara (1983)፡፡

ከሃሳቡ መረዳት የሚቻለው ትክክል የሆነው የቋንቋ ቅርፅ ትክክል ካልሆነው ቅርፅ ጋር ሲዛመድ የምዕላድ፣ የፍቺ አልያም የሰዋሰው ጉዳይ እንደሚሆን ያስረዳል፡፡

Brown (1994, 214) ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ቀደም ሲል ከተማሩት ያገኙት ቀደምት ልምድና በአዕምሯቸው የያዙትን የአወቃቀር ህግ በአጠቃላይ እንደሚሰራ አድርጎ ማምጣቱ ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ ሲታይ ከሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች እድገት የመማር ቲዎሪ ላይ የመጣ ነው ካሉ በኋላ "ስህተት ብያኔ" እና "ሽግግር" የተለያዩ ሂደቶች ሳይሆኑ ተመሳሳይ የሆኑ የቋንቋ መማር ስትራቴጂን የሚወክሉ ናቸው ይላሉ፡ሁለቱም ቢሆኑ ተማሪው አዲሱን ቋንቋ በሚለምድበት ጊዜ ስሜት እንዲሰጥ ለማድረግ ቀደም ሲል የሚያውቀውን የመጠቀም ውጤቶች ናቸው፡፡ "ስህተት ብያኔ"ሲባልም ተማሪው በታላሚው ቋንቋ ወይም በሁለተኛው ቋንቋ በሚያውቀው ህግ ሌላውን ለማጠቃለል መሞከር ሲሆን "ሽግግር" በሚባልበትጊዜ ግን ተማሪው ሁለተኛ ቋንቋውን በሚማርበት ጊዜ ሃሳቡን ለማቀናጀት በአፍ መፍቻ ቋንቋው የሚያውቀውን ቀደምት ልምድ አምጥቶ መጠቀም ማለት ነው፡፡

ከቀረበው ሃሰብ መገንዘብ የሚቻለው የስህተት ብያኔ እና ሽግግር ተማሪዎች ቀደም ሲል የሚያውቁትን ደኃራዊ እውቀት አዲሱን ቋንቋ በሚለምዱበት ጊዜ መገልገል እንደሆነ እና ተደጋጋፊ እንጂ የማይለያዩ መሆናቸውን የሚያስረዳ መሰረታዊ ሃሳብ መሆኑን መረዳት ችያለሁ።

ሆኖም Littlewood (1986, 25) እንደሚሉት ለአንድ ለተወሰነ ወይም ለተለየ ስህተት መፈጠር ምክንያቱ "ስህተት ብያኔ" ይሁን "ሽግግር"ለመለየት የሚያስችሉ ብዙ ምሳሌዎች አሉ። ሌላው ቀርቶ ቀደም ባለው ጊዜ ለስህተት ብይኔ በምሳሌነት ቀርበው የነበሩትን ነገሮች ዛሬ እንደገና ለሽግግር የሚቀርቡ መሆናቸውን ይገልፃሉ። በመቀጠልም ሌላው ለስህተት መፈጠርና ምክንያት ይሆናል ብለው ከጠቆሙት ጉዳይ አስፈላጊ ጉዳዮችን በመግደፍ አስፈላጊ ጉዳዮችን በመደጋገም ሲሆን በጥቅሉም ለስህተት መፈጠር ምክንያት ናቸው ያሏቸው፡-

- ከአፍ መፍቻ ቋንቋ የተሸጋገሩ ህጎች
- የሁለተኛ ቋንቋ አጠቃላይ ህግና ስህተት ብያኔ
- ነገሮችን መግደፍ ናቸው።

እንደርሳቸውም አባባል የመጀመሪያው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሂደት፣ የሁለተኛውና ሶስተኛው ደግሞ ውስጠ ቋንቋ ሂደቶች ናቸው።

### 2.3.3 የማስተማሪያ መሳሪያዎች እና የማስተማሪያ ዘዴ ድክመት

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለስህተት ከሚዳረጉባቸው ምክንያቶች መካከል የተሳሳተ የማስተማሪያ መሳሪያ ምርጫ እና ደካማ የማስተማር ዘዴ ይገኙበታል። እነዚህን የስህተት ምንጮች Nagara (1983, 40) ውጫዊ ተጽዕኖዎች ሲሏቸው Brown (1994, 215- 17) ደግሞ፡-

የትምህርት አውድ ችግር ይሏቸዋል። አውድ ያሉትም የመማሪያ ክፍልን፣ ከመምህሩ እና ካሉት የትምህርት መሳሪያዎች ጋር አንድ ላይ የያዘ እንደሆነ በመግለፅ ያቀርባሉ።ይህም አውድ በትምህርት ሂደት ወቅት ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ማጠናከሪያነት ከማዋል ይልቅ በትምህርቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሲያሳድር ለስህተት መፈጠር ምክንያት ይሆናል።ስህተት ምናልባት ከማስተማሪያ መሳሪያ ምርጫ ሊመጣ ይችላል። ትምህርቱ በትምህርት መሳሪያው አማካኝነት በሚተላለፍበት ጊዜ ተማሪዎች የተሳሳተ ግንዛቤ ሊጨብጡ ይችላሉ። ይህም

የሚሆነው የትምህርት መሳሪያው በጥንቃቄ ያልተዘጋጀ እንደሆነ ወይም ተማሪዎች የተሳሳተ ነገር እንዲገምቱ ፍንጭ የሚሰጥ ከሆነ ነው፡፡ በአንድ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተሳሳተ መዋቅር ወይም የቃል ፍቺ ካለ ተማሪዎች ለስህተት ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡

የቀረቡት የምሁራን ሃሳብ የሚያስረዱት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለስህተት የሚጋለጡባቸው ምክንያቶች በአገላለፅ እንደሚለያዩ ወይም ምሁራንን የሚያስማማ ወጥ አቀራረብ አለመኖሩ እና የተማሪዎች ፍላጎት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ እንደሚችሉ ነው፡፡

በተጨማሪም የትምህርቱ አቀራረብ ተጨባጭ ካልሆነና ከተማሪዎች ግንዛቤ በላይ ሆኖ ከቀረበም ተማሪዎቹ ስህተት ሊፈፅሙ ይችላሉ፡፡ የትምህርት መሳሪያዎች አደረጃጀት፣ አወቃቀር፣ መልመጃዎችና ልምዶቹ የተቀረፁባቸው ስልቶች የስህተት ምንጭ ሆነው ሊገኙ የሚችሉበት አጋጣሚ አለ Norrish (1992, 12.15),Brown (1994, 215- 17), Ricahrds (1974, 190) በማለት ገልፀዋል፡፡

የምሁራኑ ሃሳብ የሚያስገነዝበው የማስተማሪያ ዘዴዎችንበመገልገል የሚቀርበው ትምህርት ተጨባጭ መሆን እንዳለበት ነው፡፡ የማይሆን ከሆነ ግን የትምህርት መሳሪያው ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች የስህተት ምንጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ ነው፡፡

በአጠቃላይ ለስህተት ምንጭ በመሆን የሚቀርቡ በርካታ ነገሮች ያሉ ሲሆን ከትምህርት መሳሪያዎች አዘገጃጀትና አወቃቀር ጀምሮ የቋንቋ እስከ ትምህርቱን ማቅረቢያ ስልቶች ድረስ የሚኖሩት ሁኔታዎች ተጨባጭና ግልፅ ካልሆኑ የስህተት ምንጭ በመሆን ሊጠቀሱ እንደሚችሉ መረዳት የሚከብድ አይደለም፡፡

መምህራን የሚከተሉት የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎችን ለስህተት የሚዳርግበት አጋጣሚም ብዙ ነው፡፡ በመሰረቱ ማስተማርና መማር የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ መምህሩ ለማስተላለፍ የፈለገውን ሳይሆን ሌላ ነገር ሊረዱ ይችላሉ፡፡ ይህም ለስህተት ይዳርጋቸዋል፡፡ ለትምህርት የቀረቡት ይዘቶች ምንም ያህል ጥሩ ቢሆን በመምህሩ የአቀራረብ ዘዴ ጉድለትና የትምህርት ማነስ ወይም ተዘጋጅቶ አለመግባት የተነሳ የሚፈጠር ክፍተት ተማሪዎች ለስህተት ሊዳረጉ የሚችሉበት አጋጣሚ ይከሰታል፡፡ ለምሳሌ በአፃፃፍና በንበት በጣም ተቀራራቢነት ያላቸው ግን ደግሞ በትርጉም የሚለያዩ ቃላትን በተከታታይ ማስተማር ተማሪዎቹ ቀይተው በቃላቱ ለመጠቀም ሲጥሩ አንዱን በሌላ በመተካት ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ ወይም ደግሞ መምህራኑ የተሳሳተ ብያኔ ካስቀመጡ፣ የተዛባ መረጃ ከሰጡ፣ ተማሪዎች የማያውቁትን ነገር በምሳሌነት

ካቀረቡ፣ የተሳሳተ ቃልና ሰዋስዋዊ ማጠቃለያ ካሰፈሩ ተማሪዎች ሊሳሳቱ ይችላሉBrown (1994, 215,17), Littlewood (1986, 30-41) Norrish (1992, 15) በማለት ገልፀዋል።

ከላይ የቀረበው ሃሳብ የሚያስገነዝው ከትምህርት መሳሪያዎች ባለፈ መምህራን የሚከተሉት የማስተማሪያ ስነ ዘዴ በሚገባ ታሳቢ ካልሆነና ከፍተኛ ዝግጅት ካልተደረገበት የማሪዎች አረዳድ ላይ ችግር እንደሚፈጥር የሚያሳይ ነው።

## 2.3.4 ማህበራዊና ስነ- ልቦናዊ ሁኔታዎች

ተማሪዎች ከማህበራዊ እና ስነ- ልቦናዎች ጫና የተነሳ እርስ በርስ በሚያደርጉት መስተጋብር አኳያ ስህተት ሊፈፅሙ ይችላሉ። ይህንን ሃሳብ Dubin and Olshtain (1986) እንደገለፁ ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ላይ አሉታዊ አተያይን ከሚፈጥሩ ምክንያቶች አንዱ ከቋንቋ የሚገኘው ጥቅም መሆኑ ተማሪው ከቋንቋ ትምህርቱ ጥቅም አገኝበታለሁ ብሎ ካሰበ ለቋንቋ አዎንታዊ እይታን በማዳበር ቋንቋውን ለመማር ያለው ፍላጎት ይጨምራል። ከዚህ የተነሳ በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት ውስጥ የሚፈፅሟቸው ፋይዳ እዚህ ግባ የማይሉት ሆኖ ካልተገኘ የመማር ተነሳሽቱ ስለሚቀንስ በትምህርቱ ሂደት ውስጥ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ሊጨምሩ ይችላሉ።

ከላይ ከቀረበው የሊቃውንት ሃሳብ መረዳት የሚቻለው ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ የሚኖረው ጥቅም የመማር ፍላጎትና አዎንታዊ እይታን እንደሚፈጥር ነው። ጥቅም የማይሰጥ ቋንቋ ባይኖርም ለትምህርት የሚቀርበው ቋንቋ ጥቅም ሰጪ መሆን እንዳለበት ያስገነዝባል።

በሌላ በኩል Norrish (1992) ቀደም ሲል ከተጠቀሱት የስህተት ምንጮች በተጨማሪ ተማሪዎች የተለያዩ ስህተቶች እንዲፈፅሙ የሚያደርጋቸው ስነ ልቦናዊ ምክንያቶች እንዳሉ ይገልፃሉ። ይሄውም ስነ- ልቦናዊ ጉዳይ ሲባል የሚያያይዘው ከተማሪዎች የግል ጉዳዮች ጋር ሲሆን ተማሪዎች ከክፍል ውጭ ስላለው ሁኔታ በአዕምሯቸው ይዘውት የሚመጡት ጉዳይ በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት በአግባቡ እንዳይከታተሉ ያደርጋቸዋል ይላሉ።

ሃሳቡ የሚያስረዳው ተማሪዎች በአማራጭነት የሚናገሯቸው ቋንቋዎች ስላሉ በሚኖሩበት አካባቢ ወይንም ከትምህርት ቤት ውጭ የሚሰሙት ነገር ለቋንቋ ትምህርቱ ትኩረት ለመስጠት ተፅኖ አሳዳሪ ሊሆን እንደሚችል ነው።

አንድ ለትምህርት የቀረበን ቋንቋ የሚማር ተማሪ ሃሳቡን በጽሁፍ ለመግለፅ ሲሞክር ከስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች ጋር በተያያዙ ምክንያቶች ስህተት ሊፈፅም እንደሚችል Mclauglin (1988) ይገልፃሉ፡፡

በአጠቃላይ ስለማህበራዊና ስነ- ልቦናዊ ሁኔታዎች የቀረቡት የሚቃውንት ሃሳቦች የሚያስገነዝቡት በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ላይ የሚስተዋለው የተነሳሽነት ማነስ፣ ተማሪው ለታላሚው ቋንቋ የሚኖረው አመለካከት አሉታዊ መሆን፣ ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ እና በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪው መካከል በሚኖረው በባህል ግጭት ምክንያት በሚፈጠር ማህበራዊ፣ ስነ- ልቦናዊ ሁኔታዎች አለመጠቀም እና የመሳሰሉት የሚጠቀሱ እንደሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡

## 2.4 የስህተት ትንተና ዘዴ

የስህተት ትንተናን ለማካሔድ እስከ አሁን ድረስ ወጥነት ያለው ዘዴ ማግኘት አልተቻለም፡፡ በትንተናው ዙሪያ በጣም ብዙ ስልት በመፈጠራቸው የተነሳ፣ እንደስልቶቹም አይነት የስህተትን አይነቶችን በመመደቡም ላይ ልዩነቶች እየሰፉ በመምጣታቸው የስህተት ትንተናን ትልቅ እንቅፋት አጋጥሞታል Lott (1983, 256) በማለት አብራርተዋል፡፡

ስለስህተት ትንተና ዘዴ ከቀረበው ሃሳብ መረዳት የሚቻለው ስህተት ትንተና ሲደረግ ቋሚ የሆነ አተናተን ዘዴ አለመኖሩን ሲሆን በሰዎች መካከል የስህተት አመዳደብ ልዩነት እንደሚስተዋል ነው፡፡

### 2.4.1. የስነልሳን ክፍሎችን መሰረት ያደረገ ክፍፍል

በርካታ የስህተት ትንተና ዘዴዎች በስነልሳናዊ የመዋቅር ክፍሎች ላይ ተመስርተው የተጠኑ ናቸው፡፡ ጥናታቸውም በአንዱ ስነልሳናዊ ክፍል ወይም በተወሰኑት አልያም በሁሉም ላይ ሊያተኩር ይችላል፡፡ የስህተት ትንተናው በስነድምጽ፣ በስነመዋቅር፣ በቃላት፣ በስነአገባብ ፍቺ እና የዲስኩር ጠቋሚዎች ላይ ሊያተኩር ይችላል፡፡ በዚህ ዘዴ ስህተቶችን ለመተንተን የሚፈልግ አጥኚ ስህተቶችን ከለቀመና ከሰበሰበ በኂላ እንደስህተቱ አይነት በተለያየ ስነልሳናዊ ምድብ ውስጥ እያስቀመጠ ይተነትናል፡፡ በርካታ አጥኚዎችም ስህተቶችን በስነልሳናዊ መዋቅሮች በመከፋፈል እና በመተንተን ውጤታቸውን ይፋ ለማድረግ ይጠቀሙበታል፡፡ አንዳንዶቹም አጥኚዎች ይህን ዘዴ እንደበቸኛ የስህተት መተንተኛ ስልት ይቆጥሩታል፡፡ በዚህ

ዘዴ አጥኚው አስቀድሞ ለማጥናት ካቀዳቸው የስህተት አይነቶች ውጪ ለሆኑ ስህተቶች ትኩረት አይሰጥም። Duley et.al (1982:146-150)

## 2.4.2. የአረፍተ ነገር ቅርጾችን መሰረት ያደረገ ክፍፍል

በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ሂደት ውስጥ ተማሪዎች የሚጽፏቸውን አረፍተ ነገሮች ውጫዊ ቅርጽ ስንመለከት የተለያዩ አይነት ስህተቶች ያሉባቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ተማሪዎች አስፈላጊ የሆነ ዓረፍተ ነገር አካልን ሊገድፉ ወይም የማያስፈልጉትን ሊጨምሩ ይችላሉ። ከዚህም በተጨማሪ የቋንቋውን ቅርጽ አለአግባብ ሊያሰፉ የአንዱን የአረፍተ ነገር አካል ከሌላው በማስቀደም ቅደም ተከተል ሊያዛቡ ለአንድ አገልግሎት ለምሳሌ፦ ለእምርነት ሁለት ምልክቶች ሊጠቀሙ ወዘተ… ይችላሉ። በመሆኑም ይህ አይነቱ የስህተት አከፋፈል ዘዴ በአረፍተ ነገር ውጫዊ መዋቅር ላይ የሚታዩ ስህተቶችን ይመለከታል። ይህ ዘዴ አንድን አዲስ ቋንቋ ወይም ሁለተኛ ቋንቋ ለመማር ተማሪው በምን አይነት አእምሮአዊ ሂደት ውስጥ እንደሚያልፍ እና ቋንቋው ምን አይነት መንገድ ተጠቅሞ እየለመደ/እየተማረው እንዳለ የሚጠቁም መረጃ ለመስጠት ከማገልገሉም በላይ ተማሪው በሚማረው ቋንቋ ላይ የሚፈጽማቸው ስህተቶች ይብዛም ይነስም የተወሰነ ተጠይቃዊ አካሄድ ላይ የሚመሰረት እንደሆነ እንድንገነዘብ ያስችለናል።

## 2.4.3. ንጽጽራዊ ክፍፍል

ንጽጽራዊ ትንተና መሰረት የሚያደርገው የስህተት ትንተና ዘዴ የሚያተኩረው በታላሚው ቋንቋ አፈፊትና በታላሚው ቋንቋ ኢ-አፈፊት የሆኑ ተማሪዎች በቋንቋ ለመዳ እና መማር ሂደት የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች በማነጻጸር ነው። ይህንንም Duley et.al (1982) በምሳሌ ሲያብራሩ አፉን በኮሪያ ቋንቋ የፈታ ሰው እንግሊዝኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ሲማር የሚፈጽመው ስህተት እና እንግሊዝኛን በአፍ መፍቻ ቋንቋነት እየለመደ ያለ ህፃን ልጅ የሚፈጽማቸውን ስህተቶች በማነጻጸር ለመተንተን ሙከራ ሲያደርግ በንጽጽራዊ ትንተና ላይ የተመሰረተ የስህተት አከፋፈል ዘዴ መተግበር አስፈላጊ ይሆናል በማለት ገልጸዋል።

## 2.4.4. ተግባቦታዊ ተጽእኖ መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል

በዚህ ዘዴ ስህተቶች የሚከፋፈሉት ተግባቦትን ከማወካቸው አንጻር ነው። በንጽጽራዊ ትንተና እና በአረፍተ ነገር ላእላይ መዋቅር ላይ የተመሰረቱ የስህተት ክፍፍሎች በራሳቸው በስህተቶች ገጽታ ላይ የሚያተኩሩ ሲሆኑ ተግባቦትን መሰረት በማድረግ የሚከፋፈሉት ስህተቶች ግን

የሚያተኩሩት ከተግባቦት አኳያ ለአንባቢው ወይም አድማጩ መልዕክቱን በትክክል ከመረዳት ወይም ካለመረዳት አንጻር ነው፡፡

## 2.5 የስህተት ትንተና አስፈላጊነት

በተማሪዎች ድርሰት ላይ የስህተት ትንተና ማካሄድ በርካታ ፋይዳዎች እዳሉት ይገለፃል፡፡ የስህተት ትንተና ቋንቋን የመማር ማስተማር ሂደት ውጤታማ የሚሆንበትን አቅጣጫ ይጠቁማል፡፡ ይህንን በተመለከተ Rechards (1974), Ellis (1989) እና Dulay et al (1982) ሲገልጹ ከስህተት ትንተና ውጤት ግንባር ቀደም ተጠቃሚዎች የቋንቋ መምህራን እንደሆኑ ሲገልፁ፣ መምህራኑ የሚያስተምሯቸውን ተማሪዎች ዳራዊ እውቀት እንዲረዱ ያደርጋል፤ ካገኙት መረጃ በመነሳት የትኛውን ይዘት በምን ዓይነት መልክና ለምን ያህል ጊዜ ማስተማር እንዳለባቸው እንዲወስኑ ያግዛል፡፡ የማስተማር ስነ ዘዴና የማስተማሪያ መሳሪያዎች ያለባቸውን ችግሮች እንዲፈትሹ ይረዳቸዋል፤ በሌላ በኩል የቋንቋ ተማሪዎችን ሰዋስው ለማስተማር ስህተቶችን በማደራጀት እንደ መረጃ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ተጠቃሚ የሚሆኑት ደግሞ ተማሪዎች ናቸው፡፡ተማሪዎች ለታላሚው ቋንቋ ያላቸው እውቀት ምን ያህል እንደሆነ በመጠቆም ጠንክረው ቢሰሩ የትኞቹን ስህተቶች በቀላሉ እደሚያስወግዱ እና በየትኛው የቋንቋ ክፍል ላይ ትኩረት ሰጥተው መለማመድ እንዳለባቸው ያስገነዝባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ለመርሃ ትምህርት አዘጋጆች መፅሐፎችንና የተለያዩ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ለማዘጋጀት ከፍተኛ ጥቅም አለው፡፡

በተመሳሳይ Lott (1983:256) እንደሚሉት የስህተት ትንተና በይበልጥ ለመምህራን ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡

የቀረቡት ሃሳቦች የሚያስረዱት በተማሪዎች ድርሰት ላይ የስህተት ትንተና ማድረግ ለአስተማሪዎች ተቀዳሚ ጠቀሚታ እንደሚያስገኝ ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ተማሪዎችን በትክክል ለማወቅና ለመርዳት የሚያስችል ስለሆነ ነው፡፡

እንደ Sharma (1986፣ 7) የስህተት ትንተና ፈርጀ ብዙ ጠቀሜታዎች ያሉት በመሆኑ በተማሪዎች የተለያዩ ቋንቋ የመማር ሂደት ላይ ትንተና ማካሄድ በእጅጉ ይጠቅማል፡፡ የትምህርት መርሃ- ግብር መነሻ፣ መካከልና መጨረሻ የስህተት ትንተና ማድረግ ጠቃሚነቱ የጎላ ነው፡፡ በትምህርቱ መነሻ የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በታላሚው ቋንቋ ላይ ያላቸውን ዳራዊ ዕውቀት ለመገንዘብ በትምህርት መካከል የትምህርቱ ሂደት ምን ያህል በተገቢው ሁኔታ

እየሄደ መሆኑን ለመመዘን (ለመገምገም) በትምህርቱ መጨረሻ ደግሞ ተማሪዎቹ በትምህርቱ ሂደት የቀሰሙትን ዕውቀትና ያስወገዷቸውን ስህተቶች ለመገንዘብ ይጠቅማል፡፡ መምህራን በትምህረት መርሃ ግብሩ ሂደት የማስተማሪያ ዘዴያቸው ምን ያህል ውጤታማ እንደሆነ እና የትኞቹን ተማሪዎች በምን አይነት መንገድ መርዳት እንደሚችሉ የስህተት ትንተናው ሊጠቁማቸው ይችላል

ሃሳቡ የሚያስገነዝበው የስህተተት ትንተና በርካታ ጠቀሜታዎች ያሉት ቢሆንም ለትምህርቱ መርሃ ግብር ጠቃሚነቱ ከፍተኛ መሆኑን ነው፡፡ የጎላ ሉሆን የቻለውም መምራን የተማሪዎቻቸውን የቀደመ ሃብት ለማወቅ የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡

Corder (1973:25) ሲገልፁ ለመምህሩ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ችግሩጎልቶ የሚታይባቸውን የቋንቋ ይዘቶችን አውቆ ለመለየትና ከስህተቶቹ በመነሳት ችግሩን ለመቅረፍ የሚያስችለውን ዘዴ በመቀየስ የመፍትሄ ሀሳቦችን ለማፈላለግና እንዲሁም ለማስተማሪያ የሚጠቀምባቸውን የማስተማሪያ መሳሪያዎች ውጤታማነትና ብቃት ለመረጋገጥ ስለሚረዳ መምህሩ ከስህተት ትንተና የሚያገኘው ጥቅም በትንሹ የሚገመት አይደለም፡፡

የስህተት ትንተና መምህሩ ለተማሪዎቹ እርማት ለመስጠት የሚረዳው እንደሆነ የምሁሩ ሃሳብ ያስገነዝባል፡፡

ለቋንቋ ተመራማሪዎችና መርሃ ትምህርት አዘጋጆች ከፍተኛ ጥቅም እንደሚሰጥ Corder (1973: 257) ሲገልፁ ለቋንቋ ተመራማሪዎች አንድን ቋንቋ እንዴት መማር እንደሚቻልና ተማሪው ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደር የሚጠቀምባቸውን ብልሃቶችንና ቅደም ተከተሎችን በተመለከተ መረጃ ለማግኘት ይጠቅማል፡፡ በመርሃ ትምህትት ቀረፃላይ ለተሰማሩ ባለሙያዎች እና ለማስተማሪያ መሳሪያ አዘጋጆች መረጃ በመስጠት በመርሃ ትምህርት እና ማስተማሪያ መሳሪያዎች ውስጥ ለየትኞቹ ይዘቶች ቅድሚያ ተሰጥቶአቸው መደራጀት እንዳለባቸው መረጃ ይሰጣል፡፡

ከምሁራኑ ሃሳብ መረዳት የተቻለው የስህተት ትንተና ከመምህራን ባሻገር ለቋንቋ ባለሙያዎች፣ ተመራማሪዎችና መርሃ ትምህርት አዘጋጆች ጠቃሚ መሆኑን መረዳት ያስችላል፡፡

## 2.6 የቀደምት ስራዎች ቅኝት

ከዚህ ጥናት ጋር ተዛምዶ ያላቸውን ቀደምጥ ጥናቶች በመቃኘት ያላቸው መሳሳይነትና ልዩነት የቀረበበት ክፍል ነው፡፡

ደብሬ (1990) "በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚፈጽሙበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ዋና ዋናየስህተቶች አይነቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና"በሚል ርዕስ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ ዓላማውም በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚፈጽሙበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው የስህተቶች በስህተት ትንተና ዘዴ መመርመር የሚፈጽሟቸውን የስህተት ዓይነቶችና ምንጮች ለመለየት የሚል ነው፡፡ ዓላማውን ለማሳካት የጽሁፍ መጠይቅና በተማሪዎች የተጻፉ ድርሰቶች ናቸው፡፡ የጥናቱ ውጤትም የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት፣ የቋንቋ አወቃቀር ስህተቶች፣ የስርኣተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች፣ የጽንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ስህተቶች እና ለመለየት ያልታወቁ የስህተት ምንጮች መኖራቸውን ጠቁመዋል፡፡

የደብሬ (1990) ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው መነሻ ይዘታቸው፣ ሁለቱም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት መቅረባቸው እና የድርሰት ጽሁፍ ላይ ትኩረት ማድረጋቸው ሲሆን የሚለያዩበት ደግሞ ትኩረት ያደረጉበት የክፍል ደረጃ 9ኛ እና 11ኛ መሆኑ እና የተጠኑበት ዘመን (1990 እና 2015) ይለያያቸዋል፡፡

ምህረት (1998) "በዋቻሞ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሀድይኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍልተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ነው፡፡የጥናቱ ውጤትም በተማሪዎች ድርሰት ላይ የታዩ ስህተቶችም የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ሲሆኑ ለስህተቶች መፈጠር በምክንያትነት የቀረቡት መካከል የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ፣ የውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ፣ የመማር ማስተማር ድክመቶች፣ ስነ- ልቦናዊ እና ማህበራዊ ሁኔታዎች ናቸው በማለት አቅርበዋል፡፡

የምህረት (1998) ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ተመሳሳይነት ተማሪዎች ድርሰቶችን በሚፅፉበት ጊዜ የሚከሰቱ ስህተቶችን መተንተናቸውና ሁለቱም ለሁለተኛ ዲግሪ መቅረባቸው ሲሆን ሁለቱን ጥናቶች የሚለያቸው የጥናት ቦታቸው (ዋቻሞና አርሲ ቀርሳ) መሆናቸው፣

ጥናቶቹ የተደረጉበት ዘመን፣ ለጥናቱ መነሻ ያደረጓቸው ቋንቋዎች (ሃድይኛና ኦሮምኛ) እና የከተሉት የአተናተን ስልት (ገለፃና ቲ ቴስት) መሆኑ ነው፡፡

ልዑልሰገድ (1997) "በወላይትኛ እና ሲዳምኛ ተናጋሪዎች የአማርኛ ድርሰት ውስጥ የታዩ ስህተቶችና የስህተቶች ምንጭ ትንተና" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የቀረበ ጥናት ነው፡፡ ዓላማውም በአዋሳ ከተማ በሚገኙ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ውስጥ ሰርተፊኬት መርሃግብር በመማር ላይ ያሉ አፋቸውን በወላይትኛና ሲዳምኛ ቋንቋዎች የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ዋና ዋና ስህተቶችና የስህተት ምንጮች መለየት ነው፡፡ ዓላማውን ለማሳካት በመረጃ መሰብሰቢያነት የጽሁፍ መጠይቅና በተማሪዎች የተዘጋጁ ድርሰቶች ናቸው፡፡ የጥናቱ ውጤትም ለጽህፈት ትምህርት ትኩረት አለመስጠታቸው፣ የተማሪዎች የትምህርት ዳራ ደካማ መሆን፣ የመምህራን የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን ዳራ ያላገናዘበ መሆን የሚሉትና ሌሎችንም ማረጋገጥ የተቻለበት ነው፡፡ ጥናቱ ከአሁኑ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የድርሰት ስህተት ትንተና ላይ መመስረታቸው ሲሆን የተጠኑበት ዘመን፣ ቦታ፣ የይዘታቸው ስፋትና ጥበት እንዲሁም የቀደመው የሁለት ቋንቋዎች ተናጋሪዎችን ትኩረት በማድረግ በንጽጽር መልኩ የቀረበ ሲሆን የአሁኑ ጥናት ደግሞ የኦሮምኛ አፈ ፈት ተማሪዎች ላይ ብቻ ማተኮሩ እንዲለያዩ አድርጓታል፡፡

እስጢፋኖስ (2012) "በኮንስኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች እና የስህተቶች ምንጮች ትንተና" በሚል ርዕስየተዘጋጀ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ዋና አላማም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በኮንሶ ዞን በኮንስኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈጥሩትን ሰዋስዋዊ ስህተትና የስህተት ምጮችን ማሳየት ነው፡፡ በመረጃ መሰብሰቢያነት በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ርዕሶች ድርሰት እንዲፅፉ ተደርገውና ለመምህራን ቃለ መጠይቅም ተደርጎላቸው መረጃዎችን በመሰብሰብ የተዘጋጀና በዓይነታዊ የአጠናን ዘዴ የተጠና ነው፡፡ የጥናቱ ውጤትም የተማሪዎቻቸውን የስህተት አፈጣጠር ችግሮችንና ምጮቻቸውን ተረድተው የመማር ማስተማሩን ስራ ሲያከናውኑ ተገቢውን ድጋፍ ለተማሪዎቻቸው በማድረግ የመማር ማስተማሩን ስራ በተሳካ ሁኔታ ማስሄድ እንዳለባቸው ያመላከተ ነው፡፡

ከዚህ ጥናት ጋር ያዛመደውም የተማሪዎችን ስህተት መለየት ትኩረታቸው መሆኑ በዋናነት ይጠቀሳል፡፡ ከሚለያዩባቸው መካከል ደግሞ ከዘመንና የጥናት ቦታቸው በተጨማሪ የቀድሞው

ጥናት በዓይነታዊ አጠናን የቀረበ ሲሆን የአሁኑ ጥናት መጠናዊና ዓይነታዊ የአጠናን ዘዴዎችን በመከተሉ ነው፡፡

ማንጠግቦሽ (2009) በወላይታ ዞን በሶዶ ከተማ አፋቸውን በወላይትኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና በሚል ርዕስ ለኮተቤ ዩኒቨርሲቲ የቀረበ ጥናት ነው፡፡የዚህ ጥናት ዋና አላማ በሶዶ ከተማ በሚገኙ ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በወላይትኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች በስህተት ትንተና ዘዴዎች አጥንቶ ዋና ዋና የስህተት አይነቶችን መለየትና ለስህተቶቹ መፈፀም ምክንያት የሆኑ ምንጮችን መጠቆምና ማብራራት ነው፡፡ በጥናቱ የተገኘው ውጤትም በአጠቃላይ የተፈጸመውአማካይ የስህተት መጠን 44.15% እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያገናኘው የስህተት ትንተና ጉዳይ ሲሆን በተጠናበት ዘመን፣ መቼትና የአተናተን ስልት እንዲለያዩ መለያየት ችለዋል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የጥናቱ ንድፍና የአጠናን ዘዴ

ይህ ምዕራፍ የጥናቱን ንድፍ፣የትምህርት ቤት አመራረጥ ፣የክፍል ደረጃ አመራረጥ፣ የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ፣ የመምህራን ናሙና አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች እና የመረጃአተናተንዘዴ የሚሉትን ንዑሳን ርዕሶች በዝርዝር የሚያቀርብ ነው፡፡

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዓብይ ትኩረት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች እና የስህተት ምንጮችን መተንተን ነው፡፡ ጥናቱ የተከተለው የምርምር ሥልት ዓይነታዊና መጠናዊ የአጠናን ሂደትን ነው፡፡ ይህ ዘዴ የተማሪዎቹን የአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ ያላቸውን ልምድ እና ባህርይ የሚዳስስ ነው፡፡

ይህ ጥናት Ellis and Barkhiuzen (2005) ያደቀረቡትን አሰራር መሰረት አድርጎ የተሰራ ነው፡፡ በዚሁም የሚከወነው፡-

1. የተማሪዎችን የጽሑፍ ናሙና መሰብሰብ፡- ይህ የትኛው የተማሪዎች ውጤት ለትንተናው ያገለግላል የሚለው የሚወሰንበት ነው፡፡
2. ስህተቶችን መለየት
3. ስህተቶችን በየአይነታቸው መመደብ
4. የስህተቶችን ገለፃ መስጠት፡- ስህተቶችን በትክክለኛው መንገድ መግለፅን ይመለከታል፡፡
5. የስህተቶችን ግምገማ ማከናወንን ይሆናል፡፡ ይህ በሰንጠረዥ በድግግሞሽና በፐርሰንታይልመግለጽን ይመለከታል፡፡

በተጨማሪም የቅድመ ትንበያ ሥልትን በመጠቀም የስህተት ምንጮችን ለመጠቆም ጥረት ይደረጋል፡፡

## 3.2 የትምህርት ቤት አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጠው ትምህርት ቤት በኦሮምያ ክልል በአርሲ ዞን በሙኔሳ ወረዳ ቀርሳ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ የተመረጠበት መንገድም በአመቺ ናሙና ስልት

ነው። ትምህርት ቤቱ የመኖሪያና የስራ አካባቢ በመሆኑ አመቺ ስለሆነና ካለው የጊዜና የገንዘብ እጥረት ኣኳያ አዋጭ መሆኑ ስለታመነበት ነው።

## 3.3 የክፍል ደረጃ አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጠው የ9ኛ ክፍል ነው። የተመረጠበት ምክንያት ደግሞ ከፍ ሲል በቀረበው ክፍል ለመግለፅ እንደተሞከረው ለአማርኛ ቋንቋ እምብዛም ተጋልጦ ከሌላቸውና የቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ከሚኖርባቸው የገጠር ቀበሌዎች ወደ 9ኛ ክፍል አልፈው የሚመጡ ተማሪዎችን ለማግኘት ሲባል ነው። የክፍል ደረጃው በወሳኝ ንሞና ስልት የተመረጠ ሲሆን በሌሎቹ የክፍል ደረጃዎች የሚማሩ ተማሪዎችን ለማካተት አልተቻለም።

## 3.4 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የሚያተኩረው በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን ከፈቱ ተማሪዎች ላይ በመሆኑ በትምህርቤቱ በ19 የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ከሚማሩ 1330 ተማሪዎች መካከል በስርዓታዊ የዕጣ ናሙና አመራረጥ ስልት (Systematic Random Sampling Technique) 30 ተማሪዎች ብቻ ተመርጠዋል።

## 3.5 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በጥናቱ ተሳታፊ የሚሆኑ መምህራንን ለመምረጥ ናሙና አስፈላጊ ሆኖ ስላልተገኘ በሁሉም የ9ኛ ክፍል ገብተው የሚያስተምሩ መምህራን በቁጥር 3 ናቸው ሶስቱም ተወስደዋል።

## 3.6 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የጥናቱን አላማ ከግብ ያደርሳሉ ተብለው የተመረጡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በተማሪዎች የሚዘጋጁ ድርሰቶችና የመምህራን ቃለ መጠይቅ ናቸው።

### 3.6.1 የተማሪዎች ድርሰት

የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ፣ ዕድሜ፣ ልምድ (ገጠመኝ) ባገናዘበ መልኩ ድርሰት ሊያፅፉ የሚችሉ 8 አማራጭ ርዕሶች ቀርበዋል። ከዚያም የድርሰቱን አፃፃፍ በተመለከተ ገለፃ ተደርጎላቸዋል። ድርሰቶቹን ነፃ የአፃፃፍ ዘዴ (Free Writing System) ተከትለው በኢ-ልብወለድ አፃፃፍ ስርዓት ሁለት ዙር በክፍል ውስጥ እንዲፅፉ ተደረገ። የመጀመሪያውን ዙር የድርሰት መልመጃ ያለምንም ቅድመ ዝግጅት ክፍል ውስጥ በአንድ ርዕስ እንዲፅፉ ተደረገ።

የሁለተኛውን ዙር ድርሰት ደግሞ ከአንድ ሳምንት በኋላ በአማራጭ ከቀረቡላቸው ርዕሶች መካከል በአንዱ ላይ ብቻ ተዘጋጅተው መጥተው በመማሪያ ክፍል ውስጥ እንዲፅፉ በማድረግ በሶስቱ የ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን እርማቱ ተደርጓል፡፡

### 3.6.2. የመምህራን ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ በጠያቂና ተጠያቂ መካከል የሚደረግ ተራክቦ ነው በማለት ያለው (2006፣ 183) ገልፀዋል፡፡

በተጨማሪም Gray (2004) ቃለመጠይቅ ሰዎች በውስጣቸው የነበረን ሃሳብ እንዲያወጡ የሚረዳ ዘዴ ነው በማለት አብራርተዋል፡፡

ለመምህራኑ ከቀረቡላቸው መጠይቆች ለጥናቱ ጠቃሚ የሆኑ በርካታ መረጃዎች ሊገኙ ይችላሉ ብላ አጥኚዋ ታምናለች፡፡ በዚህ መሰረት የመማር ማስተማሩን ሂደት እንዲሁም ተማሪዎች ፅሁፈትን ለመለማመድ ሰለሚያደርጉት ጥረትና ለቋንቋው ስለሚኖራቸው አመለካከት ስላላቸው አስተያየት በአጠቃላይ የስህተት ምንጮቹን በተመለከተ መረጃ ለማግኘት ነው፡፡ ለመምህራኖቹ የተዘጋጀው ቃለ- መጠይቅም እንደተማሪዎቹ ሁሉ በገምጋሚዎቹ አስተያየት ተሰጥቶበት ለጥናቱ ተሻሽሎ ቀርቧል፡፡

## 3.7 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ጥናቱ በመጠናዊና ዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ የቀረበ ሲሆን የድርሰት ፅሁፎች በመጠናዊ፣ የመምህራን ቃለ- መጠይቅ ደግሞ በገላጭ መንገድ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

### 3.7.1 የድርሰት ሲጻፍ ስህተቶችን አተናተን

በተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት እንደተመለከተው ስህተቶችን ለመተንተን ሲሞከር ሁለት አበይት የስህተት መክፈያ ዘዴዎች አሉ፡፡ በዚህም መሰረት ከሁለት ዐበይት የስህተት መክፈያ ዘዴዎች መካከል ቅድመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴ Norrish (1983:81-91) ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰርተ ስህተቶቹ በሚከተለው ቅደም ተከተል ተተንትነዋል፡፡

- በእያንዳንዱ ድርሰት ውስጥ ያሉትን ቃላት በመቁጠርና ሁሉም ድርሰቶች የተፃፉባቸውን ቃላት በመደመር ድርሰቶቹ የተገኙበትን ቃላት ብዛት ተማሪዎቹ ለፃፏቸው ድርሰቶች ብዛት በማካፈል እያንዳንዱ ድርሰት የተፃፈበትን አማካይ የቃላት መጠን ማግኘት፣

- በእያንዳንዱ ድርሰት ውስጥ የተፈፀሙ ስህተቶችን ለማወቅ እያንዳንዱን ስህተት በመቁጠር አጠቃላይ ስህተቶተን ብዛት ማወቅ፣
- በአጠቃላይ የተገኙት ስህተቶችን በአጠቃላይ ለተፃፈው ድርሰት ብዛት በማካፈል አማካኝ ስህተቱን ማግኘት፣
- የስህተቶቹን መጠን በመቶ በማባዛት እና የተገኘውን ውጤት ድርሰቶቹ በተፃፉበት ቃላት መጠን በማካፈል በመቶ ቃላት ውስጥ ምን ያህል የስህተት ድግግሞሽ እንዳለ ታውቋል (Norrish 1992፡ 103-104)፡፡
- በመጨረሻም የተከሰቱትን ስህተቶች በመመርመር የስህተት ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ የተባሉትን ጉዳዮች ለመገመት ተችሏል (Norrish 1992፡ 103-104)፡፡

የጥናቱ አቅራቢም ከፍ ሲል በተጠቆሙት የስህተት አተናተን ስልቶች ትንተናው በቲ ቴስት ተሰልቶ እና በገለፃ መንገድ ውጤቱ ቀርቧል፡፡

### 3.7.2 የቃለ- መጠይቅ አተናተን

Dulal et al (1982: 140-146) እንደሚገልፁት በተማሪዎች የሚፈፀሙ የተለያዩ ስህተቶች ምክንያታቸው (ምንጫቸው) ምን እንደሆነ እርግጠኛ ሆኖ መናገር አስቸጋሪ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተማሪዎቹ በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ ለሚፈፅማቸው ስህተቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የስህተት ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ ያሉ በመሆኑ እነዚህን ስህተቶች ምህራንን ስለሚያውቋቸው ከመምህራን በኩል የሚገኙ መረጃዎች ገላጭ የአተናተን ዘዴን (Descriptive Method) በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትርጎማና ትንተና

በዚህ ምዕራፍ ስር በመርጃ መሳሪያዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች በሙሉ ቅደምተከተላቸውን ጠብቀው በመጠናዊና ዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ስልቶች ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

## 4.1. የድርሰት እርማት ውጤት ጥቅል ትንተና

| የቅድመና ድህረ ልምምድ አጠቃላይ ውጤት ትንተና | ብዛት | አማካኝ ስህተት | የተጠኚ ብዛት | የተማሪ ልይይት | የልይይት ስህተት አማካኝ |
|---|---|---|---|---|---|
| የቅድመ ልምምድ ድርሰቶች ውጤት | 2093.3 | 69.77 | 30 | 14.66 | 2.32 |
| የድህረ ልምምድ ድርሰቶች ውጤት | 2399.3 | 79.97 | 30 | 12.79 | 2.66 |

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ ሦስት እንደሚያሳየው ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው የፃፏቸው ድርሰቶች ታርመው በድምሩ 2093.3 ነው፡፡ 30 ተማሪዎችን በማፃፍ መምህራን እርማት የሰጡ ሲሆን አማካኝ ስህተታቸውም 69.77 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ የተማሪ ልይይቱ 14.66 ሲሆን የልይይት ስህተት አማካኝ ውጤቱም 2.32 ነው፡፡ የድህረ ልምምድ ድርሰቶች እርማትን በተመለከተ አጠቃላይ ድምር 2399.3 ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው እንደቅድመ ተግባር ሁሉ ተማሪዎችን ድርሰት አፅፈው እርማት ያደረጉ ሲሆን አማካኙ 79.97 ነው፡፡ የተማሪ ልይይት 12.79 ሲሆን የልይይት ስህተት አማካኙ 2.66 ሆኗል፡፡ በመሆኑም የቀረበው ትንተና ከቅድመ ድርሰት ልምምድ በተሻለ መልኩ ተማሪዎች ትምህርቱ ከተሰጣቸውና ግንዛቤ ካገኙ በኋላ የተሻለ ድርሰት መፃፍ እንደቻሉ ነው፡፡ ይህ በመሆኑም ቅድመ ላይ ከፈፀሟቸው ስህተቶች ተምረው ለተሻለ አስቦ በመፃፍ የስህተት እነሳ እንዳደረጉ የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን እንዲጠቀሙ ማድረግ አስታውሰው እንዲፅፉ ማድረግ የበለጠ ቀጣይ ላይ ለመፃፍ የሚረዳ እንደሆነ ጥናቱ ይጠቁማል፡፡

## 4.2 የቅድመና ድህረ ልምምድ የድርሰቶች ውጤት ቲ-ቴስት ስሌት (P<0.05)

| ምድብ | አማካይ | ልይይት | የነፃነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ | ዝቅተኛ ልዩነት | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ልምምድ | 69.77 | 14.66 | 1.87 | 10.2 | 5 | 26.7 |
| ድህረ ልምምድ | 79.97 | 12.79 | | | | |

## 4.3 የስህተት ውጤት ትንተና

በቅድመና ድህረ ድርሰት የመፃፍ ልምምዶች ከተደረጉ በኋላ ቀጥሎ በሚቀርበው ሰንጠረዥ ስር የቀረቡትን አራት ዋና ዋና የድርሰት ማረሚያ ነጥቦች በመከተል በአራሚ መምህራን ታርመዋል በመሆኑም የፈፀሟቸውን ስህተቶች ብዛትና የተደረገው በአግባቡ ስህተቶች ተቆጥረው የቀረቡበትና የስህተት ቅነሳውን የሚያሳይ ነው፡፡

| ተ.ቁ | የስህተት አይነት | የቅድመ ልምምድድርሰት ስህተቶች ብዛት | የድህረ ልምምድ ድርሰት ስህተቶች ብዛት | የስህተት ቅነሳ በቁጥር | የስህተት ቅነሳ በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከተማሪ ድርሰቶች ይዘት አንፃር | 80 | 70 | 10 | 33.33 |
| 2 | ከተማሪ ድርሰቶች አደረጃጀትና አወቃቀር አንፃር | 252 | 235 | 17 | 56.66 |
| 3 | ከተማሪ ድርሰቶች ቃላት አጠቃቀም (የቃላት ምርጫና የአጻጻፍ ስልት) አንፃር | 430 | 401 | 29 | 96.6 |
| 4 | ከተማሪ ድርሰቶች ሰዋስዋዊ ስርዓት አንፃር | 629 | 620 | 9 | 30 |
| አጠቃላይ ድምር | | 1391 | 802 | 589 | 216.59 |

ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ 5 የሚያሳየው በእያንዳንዱ የእርማት ይዘቶች ላይ ምን ያህል ስህተቶችን ተማሪዎች እንደሰሩ ነው፡፡ በመሆኑም ቅድመ ልምምድና ድህረ ልምምድ የድርሰት ጽሁፎች ላይ የተሰሩ ስህተቶች ተማሪዎች ከፃፉባቸው ወረቀቶች ላይ ተቆጥረው የቀረቡበትን ሁኔታ የሚያሳይ ነው፡፡የቅድመ ልምምድ ድርሰሰቶችን በተደረገው ቆጠራ በአጠቃላይ 1391 ስህተቶች ተሰርተዋል፡፡ የድህረ ልምምድ ድርሰቶችን በተደረገው ቆጠራ ደግሞ 802 ስህተቶች የተሰሩ ሲሆን የቅድመና ድህረ ልዩነት 589 ስህተቶች ናቸው፡፡ ሰንጠረዡ የሚያሳየው ከቀረቡት አራት ዋና ዋና የእርማት ይዘቶች መካከል ተማሪዎች ሰዋስዋዊ የአማርኛ ቋንቋ ስርዓት አለማወቅ ወይም ችግር ያለባቸው መሆኑን ነው፡፡ ይህንን ለማለት የተቻለውም 629

በቅድመና 324 በድህረ ልምምድ ጊዜ ከሌሎች የእርማት ይዘቶች የበለጠ ስህተት መስራቻቸውን ማወቅ ስለተቻለ ነው፡፡ ስለዚህ መምብራን ድርሰት በሚያፅፉበት ጊዜ የሰዋስዋዊ ህጎችን እንዲጠብቁ የሚያስችል ትምህርት መስጠታቸው ተገቡነት እንዳለው ጥናቱ ይጠቁማል፡፡ በይበልኝ የሰዋስዋዊ ጉዳይ ተነሳ እንጂ የቃላት አጠቃቀም ጉዳይም ትኩረት የሚያስፈልገው እንደሆነ ዘንጠረዥ ላይ መመልከት ይገባል፡፡

### 4.3.1. የውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ

የውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ ተማሪዎቹ በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ለተፈጸሙት ስህተቶች ምንጭ ይሆናሉ ተብለው ከተገመቱት መላምቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ በክለሳ ድርሳኑ ለማየት እንደተሞከረው በውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ ከታላሚው ቋንቋ /አማርኛ/ ውስብስብነት የተነሳ ተማሪዎቹ የቋንቋውን አወቃቀር በሚገባ ካለማወቃቸው የተነሳ ወይም ቢያውቁትም እንኳን ለተግባቦት ተግባር ሊያውሉት ሲሞክሩ የሚፈጸሙ የቋንቋ አጠቃቀም እና አወቃቀር ስህተቶችን ይመለከታል፡፡

### 4.3.2. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ

Norrish (1938:22) መማር የልምድ ክምችት ውጤት በመሆኑ የተማሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ልምድ ታላሚውን ቋንቋ በመማር ሂደት ላይ ጣልቃ በመግባት የስህተት ምንጭ ሊሆን እንደሚችል ይገልጻሉ፡፡ በአፍመፍቻነት የዳበረ የቋንቋ ልምድ አንድን አዲስ ቋንቋ በመልመድ ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ በማሳደር ለስህተት መፈጠር ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎቹ በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ለታዩት ስህተቶች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ በዋናነት ይጠቀሳል፤ በመሆኑም ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ የተነሳ ተጠኚ ተማሪዎቹ በድምጾች በቃላት አመራረጥ፣ በአረፍተ ነገር አመሰራረት እና በመስተዋድድ አጠቃቀም ላይ ስህተት እንደሚፈጽሙ የተሰበሰበው መረጃ ያስገነዝባል፡፡

### 4.3.3. የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶችና የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለስህተት ከሚዳረጉባቸው ምክንያቶች መካከል ታላሚውን ቋንቋ ለማስተማር የተዘጋጁት የማስተማሪያ መሳሪያዎችና የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶች እንደሆኑ በክለሳ ድርሳን ውስጥ የተዳሰሰ ነገር ነው፡፡ በመሆኑም የመምህሩ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ደካማነትና የተማሪዎቹ የትምህርት ተሳትፎ በጣም ዝግተኛ መሆን ለስህተት ምፈጠር በምክንያትነት ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡ ከስህተት ትንተናውም የተገኙ ፍንጮች በተጨማሪ

ከመምህሩ እና ከተማሪዎቹ የመጠይቅ መልሶች የተገኙት መረጃዎች የመማር ማስተማሩ ሂደት ለጽህፈት ልምምዱ ተግባራዊ አለመሆን አስተዋጽኦ እንዳለው ይጠቁማሉ፡፡ ከእነዚህ መረጃዎች ውስጥ መልመጃውን እና የመልጃውን ተግባራዊነት በሚመለከት ለቀረቡት ጥያቄዎች የተሰጡ ምላሾች ይገኛሉ፡፡

### 4.3.4. ስነልቦናዊ ሁኔታዎች

ተማሪዎቹ ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው ከተሰቡት የስህተት ምንጮች በተጨማሪ የስነልቦናዊ ሁሌታዎች ተጽእኖ ተሪዎቹ ለፈጸሟቸው ስህተቶች የስህተት ምንጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ ለማወቅ ተሞክሯል፡፡

አንድን ቋንቋ በሁተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ለቋንቋው አሉታዊ አመለካከት የሚኖራቸው ከሆነ ቋንቋውን የመልመድ ፍላጎት ስለሚቀንስ ስህተት የመፈጸም አዝማሚያ ሊጨምር ይችላል፡፡ ነገር ግን ተማሪዎቹ በሁለተኛ ቋንቋ አውንታዊ አመለካከት ካላቸው ቋንቋውን የመማር እና የማወቅ ፍላጎት ስለሚጨምር ስህተት የመስራት ሁኔታ ሊቀንስ ይችላል ሲሉ Norish (1992:18) ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎቹ ማህበራዊ መቼት ማለትም በአካባቢ ያለው ማህበረሰብ ለታላሚው ቋንቋ የሚኖረው አመለካከት በተማሪዎቹ ቋንቋውን በመማር ሂደት ላይ አውንታዊ ሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድር እንደሚችል ምሁራን ይጠቁማሉ፡፡

ከስነልቦናዊ ሁኔታዎች አንጻር በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸውን አመለካከት ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም የአማርኛ ቋንቋን ለመማርም ሆነ ለማወቅ ተጠኚ ተማሪዎቹ ያላቸውን ፍላጎት ለመረዳት ከመምህራኑ እና ከተማሪዎቹ የመጠይቅ መልሶች የተገኙ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ሲገልጹ የተወሰኑ ተማሪዎች ደግሞ ዝግተኛ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

## 4.4 የተጠኚዎች የቅድመና ድህረ የድርሰት ጽሁፎች እርማት ዝርዝር ውጤት ትንተና

በምዕራፍ ሶስት የአጠናን ዘዴ ክፍል ማቅረብ እንደተቻለው የተጠኚዎች ናሙና ሲወሰድ ሰላሳ ተማሪዎች ብቻ በእጣ ናሙና አወሳሰድ መምረጥ እንደተቻለ ተገልጿል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች የጻፏቸው ሁለት የቅድመና ድህረ ድርሰትውጤቶች ከ10 የታረመላቸው ወደመቶኛ ከተቀየረ

በኋላ የአማካኝ ውጤታቸው ከተሰራና ከተደራጀ በኋላየእርማት ውጤታቸውን በሚከተለው ቲ-ቴስት ስሌት በማስላት የሚከተውን መልክ አስይዞ ማቅረብ ተችሏል፡፡

የተማሪዎችን የቅድመና የድህረ እርማት ውጤት አባሪ ለ ላይ የቀረበ ሲሆን ይህ አሰራር የቀረበውም አባሪውን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

- Variance = $\dfrac{(x_{1}-\bar{x})^2+(x_{2}-\bar{x})^2+(x_{3}-\bar{x})^2+\dots+(x_n-\bar{x})^2}{n}$

Where xi= each items

$\bar{x}$= mean (averge)

n= totla number of observaiton (total data)

$\sum$= summation

I= 1, 2, 3, … n **(**30**)**

- Standard devation is the postive root of variance

$$Sd = \sqrt[+]{varation} = \frac{\sqrt[+]{\sum_{i=1}^{n}(x_i-\bar{x})^2}}{n}$$

$$= \text{አማካኝ ስህተት} = \frac{2093.3}{30} = 69.77$$

$$= \text{sd } \sqrt{variance} = \sqrt{69.77} = 8.35$$

$$\text{ልዩነት በመቶኛ} = \frac{\text{ልዩነት}}{\text{ቅድመ}} \times 100 = \frac{307}{2093.3} \times 100 \qquad \underline{= 14.66}$$

በአጠቃላይ ከቀረበው ስሌት መመልከት የሚቻለው አማካኝ የስህተት ብዛት 69.77፣ አማካኝ የስህተት ልዩነት 8.35 እና አማካኝ የስህተት ልዩነቱ በመቶኛ 14.66 እንደሆነ ነው፡፡ የዚህ ውጤት የሚያሳየውም ተማሪዎች ድርሰት ሲፅፉ የሚሰሯቸው ስህተቶች ሃምሳ ከመቶ በላይ መሆኑን ሲሆን ይህም የሚሰሩት ስህተት በርካታ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ ምክንያቱም 69.77 ከመቶ የተሰራው አጠቃላይ ስህተት የስህተት መጠኑ ከፍተኛ መሆን የሚያሳይ ስለሆነ

ነው፡፡የተሰሩት ስህተቶችምምንጫቸውን በትክክል ለማወቅ መምህራንን ቃለመጠይቅ በማድረግ የተገኘው መረጃ ተተንትኗል፡፡

## 4.6 ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተወሰዱ መረጃዎች ውጤት ትንተና

### 4.6.1 ከስህተት ምንጮች አኳያ የተገኙ መረጃዎች

ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ስህተት የሚሰሩ ከሆነ የስህተቶቻቸው ምንጮች ምን ምን እንደሆኑ ያውቃሉ? በሚል መምህራን ለተጠየቁት የሰጧቸው ምላሾች

መምህር አንድ፡- "የመጀመሪያው የአመለካከት ችግር (ለአማርኛ ተናጋሪዎች ብቻ የተሰጠ ነው ብሎ ማሰብ)፣ ሁለተኛው የማንበብ ችግር፣ ያለማስተዋል ችግር፣ የፃፉትን ደጋግሞ ያለማየት ሁኔታ እና ግድየለሽነት ናቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ የስህተቶች ምጮች ናቸው፡፡"

መምህር ሁለት፡- "ሁለተኛ ቋንቋቸው በመሆኑ ሃሳብ ያለመረዳት ሁኔታ ስላለ ለቋንቋው ፍላጎት ማነስ፣ አቀላጥፈው በሚናገሩትና በሚረዱት የመማር ሁኔታና ኦሮሚያ ክልል በመሆናቸው ኦሮምኛ ብቻ መነገር አለበት የሚል ማህበረሰባዊ አመለካከት መኖር ምንጮች ናቸው"

መምህር ሶስት፡- "ፍላጎት አለመኖር እና ትምህርቱን ከፖለቲካ አመለካከት አንፃር መመልከት ናቸው"ብለዋል፡፡

የቀረቡት የመምህራን ሃሳቦች የሚያሳዩት ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር የሚገናኝ የአመለካከት ችግር፣ ከፍላጎት አለመኖር የመጣ ግድየለሽነት፣ ከፖለቲካ እይታዎች አንፃር እና ማህበረሰባዊ እንቅፋቶች መኖራቸውን ከመምህራን ሃሳቦች ማግኘት የተቻለ ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በርካታ ስህተቶችን ሲሰሩ የሚስተዋሉትና የመማር ፍላጎታቸው ያዘቀዘቀ ሆኖ የተገኘው በዙሪያቸው በርካታ እንቅፋት የሚሆኑ ጉዳዮች ስላሉባቸው መሆኑን መረዳት የተቻለ ሲሆን ማህበረሰቡም ሆነ ፖለቲካው በቋንቋ ትምህርቱ ተፅዕኖ መሆን እንደሌለበት ነው፡፡ ፖለቲካዊ አካሄዱ ኦሮምኛ ቋንቋን ብቻ ትኩረት እንዲሰጡ የሚያበረታታ ከሆነ ተማሪዎች የብዙ ቋንቋዎች ሃብት እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡ ማህበረሰቡም ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋ ስላገኙ ትምህርቱን ከማያገኘው ማህበረሰብ አንፃር የተሻለ መግባባት የሚያስችላቸው መሆኑን መገንዘብና ተማሪዎችን ማበረታታት እንዳለበት ጥናቱ ያመላክታል፡፡ ሌላው ግን ሙሉ በሙሉ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖን ማጥፋት ባይቻልም ማቃለልና

ተፅዕኖውን መቀነስ ስለሚቻል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተለያዩ ጊዜያት ተማሪዎቻለው ላይ ጥናት እያደረጉ ተፅዕኖዎቻቸውን በመቀነስ የተማሪዎችን ፍላጎት መመለስ እንደሚችሉ ያሳያል፡፡

## 4.6.2 ከውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ አኳያ የተገኙ መረጃዎች

ተማሪዎች በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ ለእርስ በርስ ግንኙነት ሁል ጊዜ በብዛት ሲጠቀሙበት የሚያስውሉት ቋንቋ የትኛው ነው? ለሚለው ጥያቄ መምህራን ያቀረቧቸው መልሶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

መምህር አንድ፡- "የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ነው የሚመርጡት፣ ነገር ግን በትምህርት ያገኙትን አማርኛ ቋንቋ ጣልቃ በማስገባት የሚጠቀሙበት ሁኔታ ይስተዋላል"በማለት መግለፅ ችለዋል፡፡

መምህር ሁለት፡- "ከቤት ጀምሮ እስከ ትምህርት ቤት በኦሮምኛ ብቻ ስለሚግባቡ አፍ መፍቻቸውን ተመራጭ አድርገውታል"ብለዋል፡፡

መምህር ሶስት፡- "ለእርስ በርስ ግንኙነት የሚመርጡት ቋንቋ በተመለከተ አማርኛን መስማት ይጠላሉ፤ የሚጠቀሙት የክልሉን ቋንቋ ነው፡፡ እንዲያውም አንዳንድ ተማሪዎች አማርኛን መቀለጃ አድርገው ይጠቀሙታል፤ ይህ ግን የቋንቋን እኩልነት ካለመረዳት የሚመጣ ነው"በማለት ገልፀዋል፡፡

ውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖን በተመለከተ ተማሪዎች ከቤት እስከ ትምህርት ቤት አዘውትረው የሚገለገሉት አፍ የፈቱበትን የኦሮምኛ ቋንቋን ነው፡፡ ይህ የሚያሳየውም የውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ያለባቸው መሆኑን ነው፡፡ ተፅዕኖው ጎልቶ የሚታይ መሆኑን የሚያመላክቱ ሃሳቦች በመምህሮች የቀረቡ ሲሆን ከእነዚህ መካከል አማርኛን ከማወቅና እውቀት ከመሰብሰብ ባሻገር መቀለጃ አድርገው ሲገለገሉት መስተዋሉን መግለፃቸው ነው፡፡ በመሆኑም ቋንቋ የእገሌ ሃብት ወይም ንብረት ስላልሆነ መግባቢያነቱንና ጥቅሙን በማሰብ እንዲገለገሉ የቋንቋ ምምህራን፣ የስነ ትምህርት ባለሙያዎች እና ማህበረሰቡ ትስስራቸውን እየፈጠሩ ቋንቋዎችን የማሳደግ ድርሻቸውን እንዲወጡ ጥናቱ ያስገነዝባል፡፡

### 4.6.3 ከማህበራዊና ስነ- ልሳናዊ ሁኔታዎች አኳያ የተገኙ መረጃዎች

ተማሪዎች በአማርኛ ትምህርት ድርሰት ሲጽፉ ስህተት ይሰራሉ? የሚሰሩ ከሆነ የስህተቶችን ከከፍተኛ ጅምሮ ወደ ዝቅተኛ (ከቀላል ወደ ከባድ) በቅደምተከተል ቢነግሩን? በሚል የቀረበላቸው የ9ኛ ክፍል አማርኛ የቋንቋ መምህራን ያቀረቧቸው ምላሾች በቀጣዩ ክፍል ቀርበዋል፡፡

መምህር አንድ፡- "አዎ! ተማሪዎች የተለያዩ ስህተቶችን ይሰራሉ፡፡ ከርዕስ አመራረጥ ችግር፣ የቃላት አጠቃቀም እና ሆህያት አፃፃፍ፣ ስርዓተ ነጥቦችን በሚገቡበት ሁኔታ አለመጠቀም፣ ከሃሳብ ውጭ መግለፅ የመሳሰሉትን ስህተቶች ይሰራሉ"በማለትየሚሰሯቸውን ስህተቶች አቅርበዋል፡፡

መምህር ሁለት፡- "ስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ችግር፣ የድርሰትን ምንነትና ጥቅም ባለማወቃቸው ምክንያት ፃፉ ስለተባሉ ፍቻ የመፃፍ ሁኔታ፣ የአፃፃፍ ከፍተኛ ችግር፣ የአገላለጽ ክፍተት"ከሚሰሯቸውስህተቶች መካከል እንደሚጠቀሱ ገልፀዋል፡፡

መምህር ሶስት፡- "ሃሳብ መቀያየር፣ የቃላት አጠቃቀምና ምርጫ ችግር፣ የፊደላት ግድፈት እና ስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ክፍተት"ይታይባቸዋል፡፡

ሁሉም መምህራን ተማሪዎች ድርሰቶችን ሲፅፉ በርካታ ስህተቶችን እንደሚሰሩ የገለፁ ሲሆን ጥቂቶቹም የሆህያት አፃፃፍ፣ ቃላትና ስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ የአገላለፅ፣ የግድፈትና የመሳሰሉ በርካታ ስህተቶችን እንደሚሰሩ የገለፁ ሲሆን ጥናቱ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት መምህራን የቻርት መርጃ መሳሪያዎችን ወይም ስርዓተ ነጥቦችን፣ ሆህያትን፣ ቃላትን፣ ዓረፍተ ነገሮች፣ አንቀፆችንና አጫጭር ድርሰቶችን ትልልቅ ወረቀቶች ላይ እያዘጋጁ ቢያቀርቡት እነዚህ ችግሮች እንደሚቃለሉ ይጠቁማል፡፡

### 4.6.4 ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ አኳያ ከተጠየቁ የተገኙ መረጃዎች

በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩትን አማርኛ ቋንቋ ድርሰት የመፃፍ ችሎታቸው እንዲዳብር ምን መደረግ አለበት ይላሉ? ተማሪዎች ድርሰት እንዲለማመዱ የማስቻል ጥረቱ ምን ያህል ነው? ለሚሉት ጥያቄዎች መምህራን ያቀረቧቸው ምላሾች በሚከተለው መልኩ ቀርበዋል፡፡

መምህር አንድ፡- "ከቃላትና ዓረፍተነገር ጀምሮ ተማሪዎችን ማገዝ የበለጠ ጥሩ ነው፡፡ ዓረፍተነገሮችንና ድርሰቶችን ደጋግመው እንዲፅፉ በማድረግ፣ ድርሰቶችን ለማፃፍ በሚደረገው ጥረት የክፍለ ጊዜ እጥረት እንቅፋት ሆኖናል፡፡ በሳምንት አንድ ክፍለጊዜ ብቻ ነው የሚማሩ ይህም የሚጠበቀውን ያህል ክህሎታቸው እንዳይዳብር አድርጎታል ብለዋል፡፡ አፍ መፍታ ቋንቋቸው የሚያደርግባቸውን ተፅዕኖ የሚቀርፉበትን መንገድ መጥረግና ትምህርቱን እንዲወዱ የሚያደርጋቸውን ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል"በማለት ሃሳባቸውን ሰትተዋል፡፡

መምህር ሁለት፡- "የአማርኛ ትምህርትን በገጠራማ የኦሮሚያ ክልል የሚያስተምሩ መምህራን በቂ የሆነ የትምህርት ፈቃድና እውቀት ያላቸው ስላልሆኑ አማርኛ ቋንቋን የማስተማር ብቃትና ፈቃድ ያላቸው መምህራን እንደገና ቢቀጠሩና ከሆህያት ጀምረው የቃል፣ የሐረግ፣ የዓረፍነገር፣ የድርሰት አፃፃፍ ትምህርቶችን ቢያስተምሯቸው የሚል ሃሳብ እያቀረብሁ የትምህርት ባለሙያዎች ትምህርቱን ተማሪዎች ወደውት እንዲማሪ የሚያደርግ ስራዎች ይጠበቅባቸዋል፡፡ ምክንያቱም ቋንቋው የሚዳብር ተማሪዎች ፍላጎት ሲኖራቸው ነው"ብለዋል

መምህር ሶስት፡- "የክልሉ ትምህርት ፖሊሲ መሻሻል ያለበት መሆኑን እጠቁማለሁ፡፡ ምክንያሁም ከአምስተና ክፍል ትምህርቱን ስለሚጀምሩት የድርሰት መፃፍ ብቃታቸው እንዳይዳብር ያደረገው ነው፡፡ ሆኖም መጽሐፉ አራቱንም የቋንቋ ክህሎቶች ለማዳበር የቀረበ ቢሆንም ማንበብና መፃፍ ላይ ትኩረት ቢያደርጉ የተሻለ ነው፡፡ በመሆኑም ድርሰት የመፃፍ ችሎታ እንዲዳብር ማንበብ፣ የጽሁፍ ልምምድ ማድረግ፣ እየደጋገሙ መፃፍና የቃላትን ፍቺ ማወቅየዳበረ ጥሩ ድርሰት መጻፍ እንዲችሉ መሰራት ያለበት ነው"በማለት ገልፀዋል፡፡

ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት የመፃፍ ችሎታቸው እንዲዳብር መደረግ ስላለባቸው ጉዳዬች ለተጠየቁት ከቀላሉ ነገር ጀምሮ ማስተማር፣ ትኩረትና ክትትል ማድረግ፣ የክልሉን ትምህርት ፖሊሲ ማሻሻል፣ በገጠሪቱ የኦሮሚያ ክልል በሚያስተምሩ መምህራን ምትክ በሙያው የሰለጠነ እና እውቀት ያለው መምህር መቅጠር እንደሚያስፈልግ፣ ለአማርኛ ቋንቋ ሰፊ ስዓት መስጠት፣ ተደጋጋሚ የጽሁፍ ልምምድ ማድረግና ዘወትር ማንበብ አስፈላጊ እንደሆነ የተገለፀ ሲሆን እነዚህ ሁሉ ትኩረት የሚሰጣቸው ከሆነ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ መቀነስ ይችላል፡፡

ሌላው እርስዎ በሚያስተምሩበት የ9ኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡይዘቶችና መልመጃዎች ወይም የቋንቋ ክህሎቶች መካከል ተማሪዎች የትኞቹን እንዲያዳብሩ የሚያስችሉ

ይመስሏችኋል? ለሚለው ጥያቄ የ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰጧቸው ምላሾች በቀጣዩ መልክ ቀርበዋል፡፡

መምህር አንድ፡- "ይዘቶችን ያዘጋጇቸው የቋንቋ ባለሙያዎች በሚገባ ቋንቋውን እንዲያዳብሩ ታስቦበት የተዘጋጀ ትምህርት እንደመሆኑ፣ በይበልጥ ግን የቃላትና ሰዋስው ትምህርት እንዲዳብር ያደርጋል"በማለትገልፀዋል፡፡

መምህር ሁለት፡- "ሁሉንም ማለትም የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ፊደላት ጀምሮ የክህሎትና ሰዋስው ጉዳዮችን በሙሉ እንዲዳብሩ የሚያደርግ ነው፡፡ "

መምህር ሶስት፡- "አማርኛ ትምህርቱ ለንግግር የበለጠ የሚጋብዝ ነው፡፡ አቀላጥፎ መናገርን ያስተምራል፡፡ ተማሪዎችም እየሰባበሩም ቢሆን ለንግግር ፈጣኖች ናቸው"በማለት ሃሳባቸውን አቅርበዋል፡፡

ከመምህራን ሃሳብ መውሰድ የተቻለው የመጽሐፉ ዝግጅት ለተማሪዎች መጣኝ መሆኑን ነው፡፡ የመፅሐፍ ዝግጅት ባለሙያዎችንም በሚገባ እንዳዘጋጁት ገልፀዋል፡፡ መረዳት የተቻለውም የድርሰት ትምህርቶችን ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለማቅረብ አመቺ መሆኑን ሲሆን ከላይ የተገለፀው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ግን ድርሰቶችን ሲፅፉ በርካታ ስህተቶችን እንደሚሰሩ ያሳየ ነው፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ ተማሪዎች መካከል አልችልም፣ አማርኛ መናገርም ሆነ ድርሰት መፃፍ አሆንልኝም ብሎ የሚያስብ ሊኖር ስለሚችል ባላቸው አቅም ልክ እና የቻሉትን ያህል በማበረታታት ማገዝ እንደሚቻል ጥናቱ ጥቆማ ሰጪ ነው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና የመፍትሔ ሃሳብ

ጥናቱ በዚህ ምዕራፍ ስር የጥናቱን ውጤቶችና መፍትሔ ሃሳቦችን በማቅረብ የሚያጠናቅቅበት መሰረታዊ ክፍል ነው።

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዓላማ አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈፅማቸውን ስህተቶች እና የስህተት ምንጮችን መተንተን ነው። ከጥናቱ ዓላማ በመነሳት የጥናቱ ማጠቃለያ ሃሳብ ቀርቧል።

የተገኘው ውጤትምበቲ- ቴስት ስሌት ተሰልቶ 8.35 መሆኑ ተረጋግጧል። ውጤቱ የሚያሳየውም መምህራን ከድርሰት ልምምድ በፊትና በኋላ የሚገኘው ውጤት የተሻለ መሆኑን ሲሆን ድርሰት ሲያፅፉ ግብዓት የሚሆናቸውን ትምህርት መስጠት የሚገባ መሆኑን ነው።ከቃለ መጠይቅ የተገኘው ውጤትም ከቲ ቴስት ስሌቱ በማይጣረስ መልኩ ሲሆን ተማሪና መምህር የማይለያዩ በመሆናቸውም የ9ኛ ክፍልን አማርኛ ትምህርት ለሚያስተምሩ መምህራን ቃለመጠይቅ በማቅረብ ስለተማሪዎቻቸው ድርሰት የመፃፍ ችሎታና በሚፅፉበት ጊዜም የሚሰሯቸውን ስህተቶች የተመለከቱ ጥያቄዎች የቀረቡላቸው ሲሆን የተሰበሰበው መረጃ በሚገባ ተተንትኖ የተገኘው ውጤትም ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ተጽዕኖዎች እንዳለባቸው ማወቅ ተችሏል።

## 5.2 የመፍትሔ ሃሳቦች

የጥናቱ ትኩረት የሆኑት በቀርሳ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆን እነዚህ ተማሪዎች ከተለያዩ የኦሮሚያ ክልል አቅጣጫዎች የሚመጡ ናቸው። በመሆኑም ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ የሚገጥሟቸውን ስህተቶች በማጥናት ግኝቶችን ማስቀመጥ የተቻለ ሲሆን ከጥናቱ መሰረታዊ ግኝቶች በመነሳትየመፍትሔ ሃሳቦች ቀርበዋል።

- መምህራን ተማሪዎች ድርሰት እንዲፅፉ ሲያደርጉ ለቃላት አጠቃቀም ትኩረት እንዲሰጡና ሰዋስዋዊ የቋንቋ ህግጋትን እንዲጠብቁ ቢመክሩ፣

- በአማርኛ ትምህርታቸው ላይ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖን ለማስወገድ የቋንቋን አገልግሎትና ጥቅም በሚመለከት ግንዛቤ ቢፈጥሩ
- የተማሪዎች ድርሰት ፅሁፎች ላይ የሚታዩ ዋና ዋና ስህተቶችን እየለዩ ለማስተማሪያነት ቢጠቀሟቸው ስህተትን ለመቀነስ ስለሚረዳ ስህተቶችን በየጊዜው እየለዩ ለማስተማሪያነት ቢጠቀሟቸው፤
- ፖለቲካዊ የቋንቋ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ የክልሉትምህርት ፖሊሲ ቢሻሻልና ለቋንቋ ትምህርት ተገቢ ትኩረት ቢሰጥ፣
- መምህራን ለድርሰት የማፃፍና የማለማመድ ሂደቱን ሳይሰለቹ ቢቀጥሉበት፣የሚሉትን የመፍትሔ ሃሳቦችማቅረብ ተችሏል።

# ዋቢ መጻህፍት

ልዑልሰገድ አሰፋ። (1987)።‘ ‘በወላይትኛ እና ሲዳምኛ ተናጋሪዎች የአማርኛ ድርሰት ውስጥ የታዩ ስህተቶች እና የስህተት ምንጭ ትንተና ’’የአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። (ያልታተመ)

መሰረት ጣፋ። (2003)። በሐረማያና በአዴሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ዋና ዋና የስህተት አይነቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ፋክሊቲ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር። (ያልታተመ)

ምህረት ሳዳም:: (1998)።‘ ‘በዋቻሞ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሀድይኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና። ’’የአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። (ያልታተመ)።

ማንጠግቦሽ (2009) በወላይታ ዞን በሶዶ ከተማ አፋቸውን በወላይትኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና፣ የአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ኮተቤ ዩኒቨርሲቲ። (ያልታተመ)።

ባየይማም። (2010)። አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው (4ኛ እትም)፣ አዲሰ አበባ። አልፋ አታሚዎች።

አማረ ሰውነት። (1976)። “አፋቸውን በትግረኛ ቋንቋ የፈቱ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስነ ልሳናዊ ስህተቶች።” የአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ። አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ (ያልታተመ)።

እስጢፋኖስ (2012) “በኮንስኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች እና የስህተቶች ምንጮች ትንተና፣ አዲስ አበባ፣ አዲስአበባዩኒቨርሲቲ።

ያለው እንዳወቅ:: (2006)። የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር። አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚ።

ደብሬ ተሰማ፡፡ (1990)፡፡ “በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና፡፡” አዲስ አበባ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ (ያልታተመ)፡፡

Brown, H. Dougalas. (1994). anError Analysis of Students Composition TRAL.

Corder, S.Pit. (1973) Introducing Applied Linguistics, London: Penguin Groups Ltd.

—————— (1974) The significance of learners errors. In J,C. Richards (ed.) Error Analysis: Perspectives on Second Language Acquisition. London and New York: 5th ed. Oxford: Oxford university Press.

——————— (1967).TheSignificance of Learners Errors.IPRL.

Dubin, F and Olshtain, E (1986). Course Design: Developing Programs and Materials for Language learning. Combrige.Combrige University Press.

Dulay, H. et al. (1982). Language two. Oxford. Oxford University Press.

Ellis, R. (1989). Understanding Second Language Acquisitions. Oxford. Oxford University Press.

Gray, J. (2004). Doing Research in the Real world, Sage Publications, London: Thousands oaks; New Delhi.

Lindman, Beate, (1996).TheConcept of Error in an Analysis of Learner Language.The International Abstracting Journal for Teachers and Applied Linguistics.

Littlewood.W.T (1983).Forign and Second Language Learning, Language Acquisition Research and Implication for the Classroom. Cambrige: Cambrige University Press.

————— (1986).Foreign and Second Language Learning.Language Acquisition Research and its implications for the Classroom. Cambridge: Cambridge University Press.

Lindman.(1998). The Concept of Error in an Analysis of learner Language. Teachers and Applied linguistics: Journal for Language.

Lott David. (1983) Analayzing and Counrtacting Interference Errors, ELT.

James, C. (1996). Contrastive Analysis. New York: Longman group UK Limited.

————— (1998).Contrastive Analysis. New York: Longman group

Jakson, H. (1987). “The value of Error Analysis and its implications for Teaching and Therapy with special Reference to Panjabi Learners”. In Abdurham (ed.) Bilingualism and Bilngual. Oxford: Nter-Nelson Publishing Company Ltd.

Morrissey.M (1883) toward a grammer of Learners’ errors.IRAL.

Nagara, E.A. (1983). Non- contrastive errors in Africa English Types and Significance IRAL.

Norrish. John. (1990). Language Learners and their Errors. London Macmillan Publishers Ltd.

—————— (1992).Language Learners and their Errors. London Macmillan Publishers Ltd.

Richards, J.C and Sampson. (1974). The Study of Learner English, Error Analysis: Perspectives on Second Language Analysis, London and New York: longman group UK Limited.

Richards, J.C. (1974). Errors Analysis: Perspectives on Second Language Analysis. London and New York: Longman Group UK Limited.

Richards J.C and Schmidt R. (2002). Dictionary of Language Teaching and Applied Linguistics: Longman, rico. Chirstophe pdf.

Rivers, W.M and. Temperley, M.S. (1978).Practical Guide to The teaching of English as a Second or ForeignLanguage. New York: Oxford University Press.

Sharma, S, K. (1986). Error Analysis: Why and How? Washington: English language programs Divistion bureau of Educational and Cultural Affairs.

Sharma, S, K. (1986). Error Analysis: Why and How? Washington: English language programs Divistion bureau of Educational and Cultural Affairs.

Spolisky, Bernand. (1979). ContanstiveAnalysis and English Language Strategies of Areb Students.Language Learning.

Widdowson, H, R. (1978). Teaching Language as Communication. Oxford. Oxford University Press.

Mclaughlin,B. (1988) Theories of second Language Learning. Baltimore: Edward Arnold.

Muhammed Alfatih. (2008). Al- merikh-sc- Wikipedia Reterived from https://en Wikipedia.org/wiki Al-merrikhsc.

Wilkins. D.A. (1974).Linguistics in Language Teaching.The MIT Press Massachusetts Institute of Technology.Canbridge Massachusetts.

# አባሪዎች

**አባሪ ሀ፡- ተማሪዎች የፃፏቸው ድርሰቶች የታረሙበት ወይም መምህራን ውጤት የሰጡበት መስፈርት**


| ተ.ቁ | የትኩረት ነጥቦች | መስፈርት | የጽሁፍ ደረጃ | ነጥብ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ይዘት | ድርሰቱ ዋና ዋና ነጥቦችን ማንሳቱ፣ ተገቢ ማስረጃዎችንና ማንራሪያዎችን ማቅረቡ፣ ከሃሳብ አለመውጣቱ፣ | የጽሁፉን ዓላማ ከግብ የሚያደርሱ አስፈላጊ ነጥቦች የተነሱበት፣ የሚስብ ሁኔታ የተብራራበት መሆኑ፣<br>ይዘቶች ተብራርተው መቅረባቸው፣<br>ያልተዛመዱና እርስ በርስ የማይገናኙ ሃሳቦችን መያዙ፣ | 2.5 |
| 2 | አደረጃጀትና አወቃቀር | ሃሳቦቹ በየደረጃው ተጠየቃዊ በሆነ ቅደም ተከተል መደራጀታቸው እንዲሁም ግልፅ የሆነ የሃሳብ ተዛምዶ መኖሩ፣<br>ሃረጎችና ዓረፍተ ነገሮች ስርዓት ጠብቀው መደራጀታቸው፣ | ሃሰቦች ፍሰታቸውን ጠብቀውና ተደራጅተው የቀረቡ መሆናቸው፣<br>አንባቢን የሚስብ መሆኑ፣<br>ወቅታዊና ግንዛቤ ሰጪ የሆነ መሆኑ፣ | 2.5 |
| 3 | የቃላት አጠቃቀም<br>(የቃላት ምርጫና የአጻጻፍ ስልት) | የቃላት መረጣ፣ የአባባሎችን አጠቃቀም፣ ሆህያትን በትክክል መፃፍ፣ ድግግሽን ማስወገዱ.... | በሳል፣ ማራኪና ግብ መቺ የቋንቋ አጠቃቀም የታየበት መሆኑ፣<br>የቋንቋ አጠቃቀሙ በቂ ነው ሊባል ቢችልም አልፎ አልፎ ጉድለቶች ያሉበት መሆኑ፣<br>ከአካባቢያዊ አነጋገሮች የፀዳ መሆኑ፣ | 2.5 |
| 4 | ሰዋስው | ምዕላዶች፣ ቃላት፣ ቃላትና ሐረጋት የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ስርዓት ጠብቀው መዋቀራቸው፣ ስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም | የሰዋሰው ግድፈት የሌለበት መሆኑ፣ በሰዋስው ረገድ መልዕክቱን ለመረዳት የሚያስቸግር መሆኑ፣ በርካታ የስርዓተ ነጥቦች ችግር ያለበት መሆኑ፣ የአፃፃፍ ችግር | 2.5 |


## አባሪ ለ፡- የተጠኚዎች የቅድመና ድህረ የድርሰት ጽሁፎች እርማት ዝርዝር ውጤት


| ተ/ቁ | አራሚ 1 | | አራሚ 2 | | አራሚ 3 | | አማካኝ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቅድመ | ድህረ | ቅድመ | ድህረ | ቅድመ | ድህረ | ቅድመ | ድህረ |
| 1 | 60 | 66 | 56 | 80 | 59 | 70 | 58.3 | 72 |
| 2 | 50 | 60 | 55 | 80 | 50 | 60 | 51.6 | 66.6 |
| 3 | 70 | 66 | 60 | 75 | 70 | 85 | 66.6 | 75.5 |
| 4 | 60 | 56 | 57 | 70 | 59 | 65 | 58.6 | 63.6 |
| 5 | 60 | 67 | 56 | 70 | 80 | 85 | 65.5 | 74 |
| 6 | 80 | 85 | 55 | 85 | 75 | 80 | 70 | 83.3 |
| 7 | 80 | 90 | 80 | 90 | 75 | 80 | 78.3 | 86.6 |
| 8 | 80 | 85 | 65 | 85 | 80 | 80 | 75 | 83.3 |
| 9 | 90 | 91 | 90 | 95 | 90 | 95 | 90 | 93.6 |
| 10 | 50 | 55 | 45 | 70 | 70 | 75 | 55.3 | 66.3 |
| 11 | 50 | 55 | 45 | 70 | 45 | 80 | 46.6 | 68.3 |
| 12 | 90 | 89 | 60 | 95 | 80 | 85 | 76.6 | 89.6 |
| 13 | 90 | 91 | 85 | 95 | 85 | 95 | 86.6 | 93.6 |
| 14 | 70 | 80 | 85 | 80 | 85 | 85 | 80 | 81.6 |
| 15 | 70 | 81 | 80 | 80 | 75 | 85 | 75 | 82 |
| 16 | 80 | 75 | 79 | 85 | 60 | 75 | 73 | 78.3 |
| 17 | 90 | 95 | 90 | 95 | 85 | 85 | 88.3 | 91.6 |
| 18 | 80 | 85 | 71 | 90 | 75 | 75 | 75.3 | 83.3 |
| 19 | 60 | 65 | 55 | 90 | 45 | 75 | 53.3 | 76.6 |
| 20 | 70 | 75 | 50 | 90 | 50 | 85 | 56.6 | 83.3 |
| 21 | 60 | 75 | 55 | 70 | 50 | 65 | 55 | 70 |
| 22 | 70 | 75 | 75 | 80 | 85 | 90 | 76.6 | 81.6 |
| 23 | 70 | 75 | 75 | 75 | 69 | 85 | 71.3 | 78.3 |


| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 24 | 70 | 65 | 60 | 80 | 62 | 85 | 64 | 76.6 |
| 25 | 80 | 85 | 75 | 90 | 85 | 90 | 80 | 88.3 |
| 26 | 60 | 75 | 75 | 70 | 70 | 90 | 68.3 | 78.3 |
| 27 | 80 | 85 | 78 | 85 | 85 | 90 | 81 | 86.6 |
| 28 | 60 | 75 | 55 | 65 | 65 | 85 | 60 | 75 |
| 29 | 90 | 90 | 80 | 95 | 85 | 90 | 85 | 91.6 |
| 30 | 70 | 70 | 65 | 80 | 80 | 90 | 71.6 | 80 |

## አባሪ ሐ፦ በተማሪዎች የተጻፉ ድርሰቶች









# አባሪ ሐ፡- የመምህራን ቃለ- መጠይቅ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

# የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

## ለቀርሳ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን የቀረበ ቃለ- መጠይቅ

## የሚወስደው ስዓት 35 ደቂቃ

**የተከበራችሁ ውድ መምህራን፡-** ፈቃደኛ በመሆን ለምትሰጡኝ መረጃ ምስጋናዬ ከፍተኛ መሆኑን በመግለጽ "በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና" በሚል ርዕስ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚቀርብ ጥናት በዝግጅት ላይ እገኛለሁ፡፡በመሆኑም ምንም እንኳን አብዛኛው መረጃ ተማሪዎች በሚጽፏቸው ድርሰቶች ላይ በሚተኮር መውሰድ የሚቻል ቢሆንም በአጠናካሪ መረጃ ሰጪነት ለሚቀርቡላችሁ አምስት መሰረታዊ ጥያቄዎች ትክክለኛውን መረጃ በመስጠት ትብብራችሁን እንድታደርጉ እጠይቃለሁ፡፡

ጥያቄ ቁጥር አንድ፡- ተማሪዎች በአማርኛ ትምህርት ድርሰት ሲጽፉ ስህተት ይሰራሉ? የሚሰሩ ከሆነ የስህተቶችን ከከፍተኛ ጀምሮ ወደ ዝቅተኛ (ከቀላል ወደ ከባድ) በቅደምተከተል ቢነግሩን?

ጥያቄ ቁጥር ሁለት፡- እርስዎ በሚያስተምሩበት የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶችና መልመጃዎች ወይም የቋንቋ ክህሎቶች መካከል ተማሪዎች የትኞቹን እንዲያዳብሩ የሚያስችሉ ይመስሏችኋል?

ጥያቄ ቁጥር ሦስት፡- በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩትን አማርኛ ቋንቋ የጽህፈት ክሂላቸው እንዲዳብር ምን መደረግ አለበት ይላሉ? ተማሪዎች ድርሰት እንዲለማመዱ የማስቻል ዝግጅቱ ምን ያህል ነው?

ጥያቄ ቁጥር አራት፡- ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ስህተት የሚሰሩ ከሆነ የስህተቶቻቸው ምንጮች ምን ምን እንደሆኑ ያውቃሉ?

ጥያቄ ቁጥር አምስት፡- ተማሪዎች በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ ለእርስ በርስ ግንኙነት ሁል ጊዜ በብዛት ሲጠቀሙበት የሚያስውሉት ቋንቋ የትኛው ነው?

## አባሪ መ፡- ከቃለ- መጠይቅ የተገኘ መረጃ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ- ምረቃ መርሐ- ግብር

መምህር አንድ (ጥያቄ አንድ)፡- "የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ነው የሚመርጡት፣ ነገር ግን በትምህርት ያገኙትን አማርኛ ቋንቋ ጣልቃ በማስገባት የሚጠቀሙበት ሁኔታ ይስተዋላል"በማለት መግለፅ ችለዋል፡፡

መምህር አንድ (ጥያቄ ሁለት)፡- "የመጀመሪያው የአመለካከት ችግር (ለአማርኛ ተናጋሪዎች ብቻ የተሰጠ ነው ብሎ ማሰብ)፣ሁለተኛው የማንበብ ችግር፣ ያለማስተዋል ችግር፣ የፃፉትን ደጋግሞ ያለማየት ሁኔታ እና ግድየለሽነት ናቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ የስህተቶች ምጮች ናቸው፡፡"

መምህር አንድ (ጥያቄ ሦስት)፡- "አዎ! ተማሪዎች የተለያዩ ስህተቶችን ይሰራሉ፡፡ ከርዕስ አመራረጥ ችግር፣ የቃላት አጠቃቀም እና ሆህያት አፃፃፍ፣ ስርዓተ ነጥቦችን በሚገቡበት ሁኔታ አለመጠቀም፣ ከሃሳብ ውጭ መግለፅ የመሳሰሉትን ስህተቶች ይሰራሉ" በማለት የሚሰሯቸውን ስህተቶች አቅርበዋል፡፡

መምህር አንድ (ጥያቄ አራት)፡- "ከቃላትና ዓረፍተነገር ጀምሮ ተማሪዎችን ማገዝ የበለጠ ጥሩ ነው፡፡ ዓረፍተነገሮችንና ድርሰቶችን ደጋግመው እንዲፅፉ በማድረግ፣ ድርሰቶችን ለማፃፍ በሚደረገው ጥረት የክፍለ ጊዜ እጥረት እንቅፋት ሆኖናል፡፡ በሳምንት አንድ ክፍለጊዜ ብቻ ነው የሚማሩ ይህም የሚጠበቀውን ያህል ክህሎታቸው እንዳይዳብር አድርጎታል ብለዋል፡፡ አፍ መፍታ ቋንቋቸው የሚያደርግባቸውን ተፅዕኖ የሚቀርፉበትን መንገድ መጥረግና ትምህርቱን እንዲወዱ የሚያደርጋቸውን ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል" በማለት ሃሳባቸውን ሰትተዋል፡፡

መምህር አንድ (ጥያቄ አምስት)፡- "ይዘቶችን ያዘጋጇቸው የቋንቋ ባለሙያዎች በሚገባ ቋንቋውን እንዲያዳብሩ ታስቦበት የተዘጋጀ ትምህርት እንደመሆኑ፣ በይበልጥ ግን የቃላትና ሰዋስው ትምህርት እንዲዳብር ያደርጋል"በማለትገልፀዋል፡፡